# ሰባቱ ምስጢራተ ቤተክርስቲያን


<u>አዘጋጅ</u>

**ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ካልዓይ**

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
የሸዋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ
(፩፱፻፴፪ - ፩፱፻፹፪ ዓ.ም.)



<u>አሳታሚ</u>


በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
በሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ

**ማኅበረ ቅዱሳን**

**አዲስ አበባ**

1993 **ዓ.ም**

እንደሚሞቱ እንዲሁ በክርስቶስ ደግሞ ህያዋን ይሆናሉና፡፡»1ኛቆሮ.15.20-21



«አሁን ግን ክርስቶስ ላንቀላፉት በኩራት ሆኖ ከሙታን ተነስቷአል፡፡ ሁሉ በአዳም እንደሚሞቱ እንዲሁ በክርስቶስ ደግሞ ህያዋን ይሆናሉና፡፡»1ኛቆሮ.15.20-21



«እነሆ ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል፤ ብርቱ የሆነ በእርሱ ለእኔ ታላቅ ሥራን አድርጓልና።» ሉቃ. 1.49

# የአርእስት ማውጫ

**ርዕስ** **ገጽ**


2. **ሰባቱ ምስጢራተ ቤተክርስቲያን** ...................................................... **37**

- ምስጢረ ጥምቀት ........................................................................ 38
- ምስጢረ ሜሮን ........................................................................ 46
- ምስጢረ ቁርባን ........................................................................ 48
- ምስጢረ ክህነት ........................................................................ 54
- ምስጢረ ንስሐ ........................................................................ 61
- ምስጢረ ቀንዲል ........................................................................ 64

ምስጢረ ተክሊል ........................................................................ 66

# ሰባቱ ምሥጢራተ ቤተክርስቲያን

ከብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ቀዳማዊ

ምሥጢር ማለት ድብቅ፣ ሽሽግ፣ ለልብ ወዳጅ ለቅርብ ዘመድ ካልሆነ በቀር የማይገለጥ ማለት ነው:: በንባብ የተሰወረ ብሂል ምሥጢር ይባላል፣ ምሥጢር አዋቂ እንዲሉ:: አስማምቶና አራቆ የሚተረጉመው ሊቅ የሰው አእምሮ አስቦና መርምሮ የማይደርስበት የአምላክ ህላዌ የአምላክ ግብርም ምሥጢር ይባላል:: «ምሥጢረ ሥላሴ፣ ምሥጢረ ሥጋዌ» ማለት ስለዚህ ነው::

በሃይማኖት ሥርዓት የጥንት አረማውያን የሚያሚርቱበትን የምትሐትና የጥንቆላ ዘዴ /ሚስቴርዮን/ ምሥጢር ይሉት ነበር:: ከሕዝብ የተደበቀ ማለት ነው እንጂ እነሱስ ያውቁታል:: በብሉይ ኪዳን፣ ምሥጢር የሚል ስም ባይሰጠውም የሚሠዋው መሥዋዕት ምሥጢርነት ነበረው፣ ኃጢአትን ለማስተሥረይ ከእግዚአብሔር ለመታረቅ የሚደረግ ነውና::

ምሥጢር ሊያሰኘው የሚችለው መሥዋዕቱን እግዚአብሔር እንዴት እንደሚቀበለው አይታይም፣ ተቀብሎም ሥርየትን መስጠቱ በእምነት እንጂ በዓይን አይታይምና፤ ከኾነ በላይ እንጂ ያን ጊዜ አይታይምና ነው::

ቤተክርስቲያን የመንፈስ ቅዱስ የጸጋው ግምጃ ቤት ስለሆነች በመስቀል ላይ የተሰጠውን አምላካዊ ጸጋ በእምነት ለሚቀርቧት ሁሉ ታድላለች፣ ትምህርቷን አምነው የተቀበሉ ሁሉ የዚህ ጸጋ ተካፋዮች ናቸው ይህን ጸጋ ለምእመናን የምታድልባቸውን መሣሪያዎች ምሥጢራት ትላቸዋለች:: ምሥጢራት መባላቸውም ስለ ሦስት ነገር ነው፣

ሀ. ሳመኑ እንጂ ሳላመኑ አይሰጡምና፣
ለ. በዓይን የሚታየው በእጅ የሚዳሰሰው ግዙፍ ነገር በመንፈስ ቅዱስ ሲለወጥ አይታይምና፣
ሐ. ምእመናን በዚህ በሚታየው የማይታየውን የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ ሲቀበሉ አይታይምና:: ይህም የሚፈጸመው በግብር አምላካዊ ስለሆነ ምሥጢር ይባላል::

የቤተክርስቲያን ምሥጢራት ሰባት ናቸው እነሱም:-

1. ምሥጢረ ጥምቀት
2. » ሜሮን
3. » ቁርባን
4. » ንስሐ
5. » ቀንዲል
6. » ክህነት
7. » ተክሊል ናቸው።

ሰባት መሆናቸው ወይም መባላቸው የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ በእነዚህ ብቻ ይወሰናል ማለት አይደለም። መንፈስ ቅዱስ አይወሰንም፣ ለስጦታውም ገደብ የለውምና /ዮሐ.3÷8/። ነገር ግን ሊቃውንት በፊት ጌታ፣ በኋላም ሐዋርያት ሥራ የሠሩባቸውን ከቅዱሳት መጻሕፍት ለቅመው ሰባቱን ምሥጢራት በቤተክርስቲያን መድበዋል፣ እነዚህ ሰባቱ እንደ አርእስት ናቸው።

አንዳንድ ሰዎች የሰባቱን ምሥጢራት ቁጥር ከፍና ዝቅ በማድረግ ይናገራሉ። በቤተክርስቲያን ታሪክ ግን ምንም እንኳ ከሊቃውን ት ብዙዎቹ ሰባቱን በሙሉ ቆጥረው ባያቀርቡም ሁለቱን አንዱ ሦስቱን ሌላው እያደረጉ ጽፈዋቸዋል። ቤተክርስቲያንም ምሥጢራትን ሰባት ናቸው ብላ የምታስተምረው በምሳሌ ሰሎሞን ጥበብ ቤቷን ያቆመችባቸውን ሰባት አዕማድ ምሳሌ አድርጋ ነው። /ምሳሌ.9÷1/
ከነዚህ ከሰባቱ ሦስቱ ማለትም
ሀ. ምሥጢረ ጥምቀት
ለ. » ተክሊል
ሐ. » ክህነት አይደገሙም። ሌሎቹ አራቱ ግን እንደየሁኔታው ይደገማሉ። እያንዳንዱን ምሥጢር መጽሐፍ ቅዱሳዊ አመሠራረትና በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን እንዴት እንደሚሠራባቸው በየተራ እንገለጣለን።

## 1. ጥምቀት፡—

«አጥመቀ» ከሚለው የግእዝ ግሥ የወጣ ነው። ፍቺውም በገቢር መንከር፣ መድፈቅ፣ መዝፈቅ፣ በተገብሮ መነከር፣ መደፈቅ፣ መዘፈቅ፣ ሙላ አካልን በውኃ ውስጥ ማስገባት ማለት ነው። ዮናናውያን /ባፕቲዝማ/ ይሉታል፤ ፍቺው አይለወጥም። የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት በንባቡ መሠረት የሚያጠምቁት በመድፈቅ በማጥለቅ ነው። ምዕራባውያን ግን /በንዝሐት/ በመርጨት ነው። ይህም «ወእንዘ ታጠምቅዎሙ» /ማቴ.28÷19/ ያለውን ንባብ ከነምሥጢሩ ያፈልሰዋል ይንደዋል። ጥምቀት በሰዋሰው አወጣጥ መድፈቅ መዝፈቅ ማለት ነው ብለናል።

በምሥጢር ደግሞ ብዙ ምሳሌዎች አሉት። ምሳሌ፡– ከአንድ አገር ወደ ሌላ መሄድ «የአብርሃም ከሀገሩ መውጣትና ወደ ከነዓን መግባት፣ የጥምቀት ምሳሌ ነው። ምእመናን ከዓለመ ኃጢአት ወጥተው የመንግሥተ

ሰማያት ዜጎች የሚሆኑት በጥምቀት ነውና:: ኖኅ ከማየ ሥራዌ ከማየ አይህ የዳነበትን መርከብ ቅዱስ ጴጥሮስ የጥምቀት ምሳሌ ናት ብሏታል:: /ቀዳ.ጴጥ.3÷21/ ምእመናን ከኃጢአት ከጥፋት የሚድኑ በጥምቀት ነውና:: ቅዱስ ጳውሎስም እሥራኤል ከግብጽ የባርነት ቀንበር ተላቀው የኤርትራን ባሕር ተሻግረው ወደ ምድረ ርስት ያደረጉትን ጉዞ የጥምቀት ምሳሌ አድርጎ ተናግሯል፤ /ቀዳ.ቆሮ.10÷1–2/፤ ምእመናን ባሕረ ኃጢአትን ተሻግረው ምድረ ርስት መንግሥተ ሰማያትን የሚወርሱት በጥምቀት ነውና:: ዳግመኛም ይኸው ቅዱስ ጳውሎስ ጥምቀትን በሞትና በመ ቃብር ይመስለዋል:: /ሮሜ.6÷3–4፣ ገላ.3÷27፣ ቆላ.2÷12/ በሞት ጊዜ ነፍስና ሥጋ እንደሚለያዩ በጥምቀትም አሮጌው ሰውነት ይሞታል ይቀበራል፤ አዲሱን ሰውነት አዲሱ ሕልውናውን ይጀምራልና:: ከሁሉ በላይ ደግሞ ራሱ መድኃኒታችን ጥምቀትን «እንደገና መወለድ» ብሎታል /ዮሐ.3÷3/:: ከአብራክ መንፈስ ቅዱስ ከማኅፀነ ዮርዳኖስ ካልተወለዱ መንግሥተ ሰማያት መግባት የማይቻል መሆኑንም ራሱ አስረድቶናል /ዮሐ.3÷5/::

ቤተክርስቲያን አሕዛብን ሁሉ እንድታስተምርና እንድታሳምን፣ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እንድታጠምቅ ታዛለች /ማቴ28÷19/:: ጥምቀት አንድ ነው አይደገምም፣ ይሁን እንጂ በምሥጢረ ሥላሴና በምሥጢረ ሥጋዌ ከቤተክርስቲያን የተለየ እምነት ያላቸው ሰዎች የሚያጠምቁት ጥምቀት እንዲከለስ ሠለስቱ ምእት አዘዋል «ለዘተወልደ እምጳውሎስ ሳምሳጢ ካእበ ያጥምቅዎ»/ የሠለስቱ ምእት ቀኖና 19፣/ ዛሬም በምሥጢረ ሥላሴ የማያምኑ ጆሆቫውያንም ሆኑ ሌሎች የሚያጠ ምቁት ጥምቀት በቤተክርስቲያን ተቀባይነት የለውም::

በሐዋርያት ጊዜ ጥምቀት የሚፈጸመው ከማስተማርና ከንስሐ በኋላ ነው /የሐዋ.ሥ.2÷38/:: ተጠማቂዎቹ ከቤተ አይሁድ ወይም ከአረማውያን ወገን ስለ ነበሩ ክርስቲያን ለመሆን ሲመጡ አዲሱን ሃይማኖት ገልጦ ማስተማርና አብራርቶ ማስረዳት፣ ካለፈው ክፉ ሥራቸው በንስሐ እንዲመለሱ መምከር አስፈላጊ ነበርና:: በጥምቀት ከኃጢአታቸው ከተለዩ በኋላ የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ የሚቀበሉት ሐዋርያት እጃቸውን ሲጭኑባቸው ነበር:: /የሐ.ሥራ.8÷14–17/

ከሐዋርያት በኋላ፣ ሕጻናትን ማጥመቅ እስከተጀመረበት እስከ አምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ የነበረው የጥምቀት ሥርዓት ደግሞ እንደሚከተለው ነው:: ወደ ክርስትና የሚመጡ ሁሉ ሦስት ዓመት የክርስትናን ትምህርት ይማራሉ:: ሲኖዶስ 8÷32:: ቀኖና ኒቅያ አንቀጽ 14 እስኪጠመቁ ድረስ ወደ ቁርባን አይቀርቡም:: በቅዳሴ ጊዜ ፃኡ ንዑሰ ክርስቲያን እስኪባል ቆይተው ፍሬ ቅዳሴው ሲጀምር ከቤተክርስቲያን ወጥተው ይሄዳሉ:: /ዲድ.9/ እንዲጾሙም ታዟል፣ /ዲድ.7/ ሦስቱን የትምህርትና የቀኖና ዘመናቸውን ሲፈጽሙ ለመጠመቅ ይፈቀድላቸዋል:: የጥምቀትም ጊዜና ሥርዓት እንደዚህ ነበር:: ምን ጊዜም ጥምቀት የትንሣኤ ሌሊት ነው:: ይህም የሆነበት ምክንያት ጥምቀት የሞትና የትንሣኤ ምሳሌ ስለሆነ ነው:: /ሰሚያሙ ወንጌለ ኵሉ መዋዕለ ያንብ ሩ

ዕዶ ኅዕሌሆሙ፣ ወይርቅይዎሙ፣ ወጥምቀቶሙሰ በመዋዕለ ፋሲካ፣ /ዲድ.26/ ከመጠመ ቃቸው ጥቂት ቀደም ብሎ የሠለስቱ ምእትን አንቀጸ ሃይማኖት በ ቃቸው አሰምተው ያነባሉ፣ ከዚያም ሦስት ጊዜ «እክህደከ ሰይጣን አአምነከ ክርስቶስ» እያሉ ከሰይጣን መለየታቸውን፣ ከክርስቶስ ጋር መዋሐዳቸውን በይፋ ይመሰክራሉ /ለዘይፈቅድ ይጠመቅ ይምህርዎ ያውግዝ ሰይጣነ ወይእመን በክርስቶስ ዲድ.39/ ከዚህ በ ኋላ ቅብዐ ቅዱስ ይቀቧቸዋል:: ሥርዓቱ ከተከናወነ በ ኋላ «አጠምቀከ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ» እያሉ ሦስት ጊዜ ብቅ ጥልቅ እያደረጉ ስም ይሰይሟቸዋል:: ሦስት ጊዜ ከውኃው ብቅ ጥልቅ አድርጎ ማውጣት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሦስት መዓልት፣ ሦስት ሌሊት በከርሰ መ ቃብር አድሮ የመነሣቱ ምሳሌ ነው:: /ሮሜ.6÷3–5/ አንድም ምእመኑ በመጠመቁ የትንሣኤ ዘለሕይወት ተካፋይ መሆኑን ለመግለጽ ነው:: ተጠምቀው ሲወጡ ኤጲስ ቆጶሱ እጁን ይጭንባቸዋል:: የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ ይቀበላሉ:: ኋላ ግን ምእመናን እየበዙ ሲሄዱ ኤ ጲስ ቀጶሳት በየቦታው ስለማይገኙ መግቦት እንዳይቋረጥ ኤ ጲስ ቆጶሳቱ ሜሮን አፍልተው ለየአብያተ ክርስቲያናቱ በማደል፣ ተጠማቂዎቹ በቄሱ እጅ ሜሮን መቀባት ይጀም ሩ /ሲኖዶስ 7÷22/ ከዚህ በ ኋላ አዲስ ነጭ ልብስ ያለብሷቸዋል:: አሮጌው ልብስ የሰይጣን የባርነት፣ አዲስ ልብስ የክርስቶስ የነፃነት ምሳሌ ነው /ሮሜ.6÷13–14፣ ገላ.3÷27፣ ቆላ.3÷9–10፣ ኤፌ.4÷24/ ይህም የቆየ የቤተክርስቲያን ሥርዓት ነው:: ለምሳሌ በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበረው ታላቁ ቁስጠንጢኖስ በሞት ጻዕር እንዳለ ተጠምቆ በተጠ መቀበት አዲስ ልብስ መቀበሩ ይነገራል:: በመጠመቂያው ዙሪያ የተሰበሰቡ ምእመናንም በየተራ ይስሟቸዋል:: ከእንግዲህ በ ኋላ «ወንድማችን ነህ፣ እኅታችን ነሽ» እያሉ:: አሮጌና ያደፈ ልብስ በብሉይ ኪዳንም የኃጢአት ምሳሌ ነበር:: አዲስ ልብስ ግን የክብር የተሐድሶ ምሳሌ ነው:: /ዘካ.3÷/

በቤተክርስቲያን ጥንትም ሆነ አሁን የጥምቀት ዕድሜ አልተወሰነም:: የጥንት ክርስቲያኖች ግን ጥምቀት ማለት «ከኃጢአት መለየት እንደገና መወለድ ማለት ነው» ያለውን ይዘው ከተጠመቁ በ ኋላ ተመልሰው ኃጢአት እንዳይሠሩ በመፍራት እምነቱን አስቀድመው ቢቀበሉም የሚጠመቁት ሊሞቱ ሲሉ ነበር:: /የቆስጠንጢኖስ ታሪክ እንደሚያስረዳው የክርስትናን እምነት ቀደም ሲል ቢቀበልም የተጠመቀው በደዌ ዳኛ በአልጋ ቁራኛ ሲያዝ ነው:: እስከዚህም የቆየበት ምክንያት ተመልሶ ኃጢአት እንዳይሠራ ስለፈራ ነው::/ ከአምስተኛውና ከስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ ግን ክርስቲያኖች እየበዙ ሄዱ:: ቤተሰቦቻቸውንም ራሳቸው ማስተማር ጀመ ሩ: ከአይሁድና ከአረማውያን አዲስ ከሚጠመቁት በቀር ከላይ ያየነው ችግር ቀርቶ ሕፃናትን ማጥመቅ ተጀመረ:: ከጥምቀት በፊት አማኞች ሊፈጽሟቸው የሚገባቸውን «ትምህርት፣ እምነት፣ ንስሐ» የተባሉትን ንባቦች ይዘው፣ በፕሮቴስታንት ማኅበር ያሉ አንዳንዶች «ሕፃናት ሳይማሩና የሚያመልኩትን ሳይመርጡ ማጥመቅ ትክክል አይደለም» ይላሉ::

ነገር ግን ቤተክርስቲያን ሃይማኖት የእግዚአብሔር ስጦታ መሆኑን ስለምታውቅ ይህን በማድረጓ አልተሳሳተችም:: እዚህ ላይ የምናስታውሰው እነዚያን ጌታ በመዋዕለ ትምህርቱ የባረካቸውን ሕፃናት ነው:: ወላጆች ልጆቻቸውን ለማስባረክ ይዘው ሲቀርቡ ትምህርቱን በጥሞና ያዳምጡ የነበሩ ሐዋርያት አይተው «በቁም ነገር መካከል እነዚህን አእምሮ ያላወቁ ሕፃናት ለምን አመጣችሁ» ብለው ተቆጧቸው:: ጌታ ግን ሐዋርያት ያልጠበቁት መልስ መለሰ:: «ተዋቸው ወደ እኔ ይምጡ» ብሎ ባረካቸው መንግሥተ ሰማያትም እንደነሱ ላሉ የምትሰጥ መሆኗን ተናገረ:: /ማቴ.19÷13–15/ ማር.10÷15፣ ሉቃ.18÷15–17:: ለእመ እግዚአብሔር አጽደቀ መኑ ዘይኬንን /ሮሜ.8÷34/ እግዚአብሔር ያጸደቀውን አልተማርህም አላወቅህም ብሎ የሚያማው ማነው? እግዚአብሔር ድምጽን ካላሰማ ሰው በዕውቀቱ እግዚአብሔርን ለማወቅ አይችልም:: እግዚአብሔር ሰውን ይመርጣል እንጂ ሰው እግዚአብሔርን አይመርጥም:: /ዮሐ.15÷16/ ሰው አምላኩን ለመምረጥ ቢቃጣ የሚመርጠው አምላክ ጣዖት ነው እንጂ እውነተኛ አምላክ አይደለም፤ የሰው ስሜት ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር የተለየ ስለሆነ:: መዳን ከእግዚአብሔር ቸርነት የሚፈልቅ እንጂ በሰው ትምህርትና ዕውቀት የሚገዛ የገበያ ዕቃ አይደለምና:: በምሳሌነትም ብንወስደው ጥምቀት በግዝረት ምትክ የተሰጠ ሕግ ነው:: አብርሃም በእግዚአብሔር ባመነ ጊዜ በጣም ሸማግሌ ነበር:: ነገር ግን ለማመኑ ምልክት እንዲሆን ተገዘር ስለተባለ በዚያ በሽምግልናው ወራት ተገዘረ:: ከሱም በኋላ ዘሮቹ በተወለዱ በስምንተኛ ቀናቸው ሲገረዙ ኑረዋል:: በዚህ መሠረት ግዝረት በብሉይ ኪዳንም የማመን ምልክት ነው:: «መነኩሴ በቆቡ፣ ወንበር በክታቡ እንደሚታወቅ» የአብርሃም ዘሮች የሆኑ ሁሉ በስምንተኛ ቀናቸው የሚገረዙት የአብርሃም ልጆች በመሆናቸው ከአብርሃም እምነት እንደማይወጡ ስለታወቀ ነው:: በቤተክርስቲያንም የኃጢአትን ሸንኮፍ ቆርጦ የሚጥለው ጥምቀት ለሕፃናት መስጠቱ ከክርስቲያን ቤተሰቦች ስለተወለዱ ሃይማኖታቸው ከእናት ከአባቶቻቸው ያለዚያም በጥምቀት ጊዜ አደራውን ከሚወስዱት ከክርስትና እናትና አባቶቻቸው የሚማሩት ስለሆነ ነው:: /የምዕራብ ቤተክርስቲያን አባት አውግስጢኖስ /395 – 430/ የሕፃናት ጥምቀት በሐዋርያት ጊዜም እንደነበረ ተናግሯል::/

አውግስጢኖስ ይህን ያለበት በቂ ምክንያት አለው:: ጥንቱን ጌታ ሐዋርያትን ሲያዛቸው «አሕዛብን ሁሉ አጥምቁ አስተምሩ» አላቸው እንጂ ሕፃን ሽማግሌ አላለም:: ዕድሜ አልወሰነም:: /ማቴ.28÷19/ ሐዋርያትም ሲያስተምሩ «በክርስቶስ እመን፣ አንተም ቤተሰብህም ትድናላችሁ» እያሉ ነው:: /የሐዋ ሥራ.16÷31/ ዋናው ካመነም ቤተሰቡንም ሁሉ ይዞ ነውና /ዮሐ.4÷53/

የጥምቀት ባሕርይዋ ዓላማዋ አንድ ሲሆን ሦስት ዓይነት አካላት እነሱም፣

ሀ. የመጀመሪያው፣ እዚህ ላይ እንዳየነው በመንፈስና በውኃ መጠመቅ ነው::

ለ. ሁለተኛው በመንፈስ ቅዱስና በእሳት መጠመቅ ነው:: «አንትሙስ ትጠመቁ በመንፈስ ቅዱስ /የሐዋ.ሥ.1÷5/ እናንተስ በመንፈስ ቅዱስ ትጠመ ቃላችሁ» ባላቸው መሠረት ሐዋርያት መንፈስ ቅዱስን በእሳት አምሳል ተቀብለው ተጠምቀዋል:: /የሐዋ.ሥ.2÷3/ አንዳንዶቹ ግን ዮሐንስ መጥምቅ «በመንፈስ ቅዱስ ወበእሳት» ያለውን፣ ያለ አግባቡ «ወ» ን ወሚመ «አማራጭ፣ ያለዚያም» ብለው ፈተው «እሺ ብትሉ በመንፈስ ቅዱስ ያለበለዚያም በውኃ» ብለው ይተረጉማሉ::እሳት በሆነው በመንፈስ ቅዱስ ተብሎ ቢፈታ እንጂ «እሳት» የመንፈስ ቅዱስ ተ ቃራኒ አይደለም:: እንዲያማ ከሆነ ሐዋርያትን እሳት በላቸው ማለት ነዋ፣ ሊ ቃውንትም መንፈስ ቅዱስን በእሳት መስለው ይናገራሉ:: ለምሳሌ የኢሳይያስን ለምጽ ያነጻውን የከሰል ፍም ሊ ቃውንት የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ አድርገው ተርጉመውታል:: /ኢሳ.6÷6–7/

ሐ. ሦስተኛው የጥምቀት ዓይነት በደም መጠመቅ ነው:: የክርስትናን ትምህርት በመማር ላይ እንዳሉ ወይም ተምረው አምነው ከመጠመ ቃቸው በፊት ያለዚያም ሁሉንም ሳያውቁት በተለያየ ምክንያት ክርስቲያኖች በሰማዕትነት ሲያልቁ በማየታቸው ተመስጠው፣ «የእነዚህ ሰዎች አምላክ እውነተኛ ነው» ብለው በሰማዕትነት የሚሞቱ ሰዎች ደማቸው ማየ ጥምቀት ይሆንላቸዋል:: በቤተክርስቲያን ሥርዓትም መጽሐፈ ኪዳን /2÷3/ የአቡሊዲስ ቀኖና 19 የግብጽ ቤተክርስቲያን ሥርዓት 44 ጥምቀት የመፈጸም መብት ያላቸው ቀሳውስትና ኤ ጲስ ቆጶሳት ብቻ ናቸው:: /ዲያቆን፣ ኢያጥምቅ ኢያቁርብ በእዴሁ ዘእንበለ አምጽዋዕ በእርፈ መስቀል 31÷2/ «ዲያቆን ለማጥመቅም ሆነ በእጅ ለማቁረብ አይፈቀድለትም:: በዕርፈ መስቀል ከጽዋው እየጨለፈ ደሙን ያቀብል እንጂ» በሐዋርያት ጊዜ ግን ዲያቆንም መደበኛ ሆኖ ያጠምቅ ነበር:: /የሐዋ.ሥ. 8÷12–38፣ በመለካውያን ሥርዓት በድንገተኛ ምክንያት ሕፃኑ የመጠመቂያ ቀኑ ሳይደርስ ቢታመምና ለሞት ቢያሰጋ ለጊዜው ኤ ጲስ ቆጶስ ወይም ቄሱ ባይገኙ ዲያቆኑ ያጠ ም ቃል፣ ዲያቆኑም ቢታጣ የሕፃኑ እናት፣ ወይም አባቱ «በሥላሴ ስም ተጠመቅ» እያሉ በአየር ላይ ሦስት ጊዜ ከፍና ዝቅ ያደርጉታል፤ ሕፃኑ ከሞት የተረፈ እንደሆነ ግን ጥምቀቱ እንደገና በሥነ ሥርዓት ይፈጸማል:: የማጥመቂያ ቦታ ሁልጊዜ ቤተክርስቲያን ናት፤ ተጠማቂ ከበዛ ግን በወንዝም በባሕርም ቢሆን ይፈጸማል::

የምሥጢራት መግቢያ በር ስለሆነው ስለምሥጢረ ጥምቀት አመሠራረትና አፈጻጸም አጠ ቃ ይ አቅዋም በመጠኑም ቢሆን ከዚህ በላይ አውስተናል:: አሁን ደግሞ ጥምቀት በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን እንዴት እንደሚሠራበት እንመለከታለን:: በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሥርዓት ወንድ ልጅ በተወለደ በአርባ ቀኑ፣ ሴት ልጅ

በተወለደች በሰማንያ ቀኗ ይጠመ ቃሉ:: የሕፃኑ ጤንነት የሚያሰጋ ከሆነ ከዚያም በታች ይሆናል። በአንዳንድ አጋጣሚ ችግር ቢዘገይም ቤተክርስቲያን ወደሷ የመጡትን አትመልስም:: ባርባ ቀን በሰማንያ ቀን የሆነበት ምክንያት በመጽሐፈ ኩፋሌ /በምዕራፍ 4÷8/ «አዳም በተፈጠረ በአርባ ቀኑ የፈጣሪውን ጸጋ ተጐናጽፎ በገነት እንዲኖር ተፈቅዶለት ነበር፣ ሔዋንም በተፈጠረች በሰማንያ ቀኗ ብርሃን ተጐናጽፋ በገነት እንድትኖር ተፈቅዶላት ነበር:: በተሳሳቱ ጊዜ ግን ይህን ክብር ተገፈፉ» የሚል ትምህርት በመኖሩ ነው:: በክርስቶስ ሞት በተደረገው እርቅ ደግሞ አዳምና ሔዋን ወደ ጥንት ቦታቸው እንዲመለሱ ተፈቅዶላቸው የአዳምና የሔዋን ልጆችም እንደየጾታቸው በአርባ በሰማንያ ቀናቸው ሲጠመቁ በዘር ከወረደው መርገም ይገላገላሉ:: የቀደሙ ወላጆቻቸው ያስወሰዱት የጸጋ ልጅነት በጥምቀት ይመለስላቸዋል:: ከቀኑ አቆጣጠር በቀር ይህ በሁሉ የታወቀ የቤተክርስቲያን ትምህርት ነው:: ከዚህም ሌላ ወንድ የወለዱ ባርባ ቀን ሴት የወለዱ በሰማንያ ቀን ሕፃኑን ወደ ቤተመቅደስ ማቅረብ እንዳለባቸው በኦሪት ታዟል /ዘሌዋ.12÷1-8/:: /ወንድ የወለዱ ሴቶች ከደመ ሕርስ የሚነጹት ባርባ ቀን ነው፣ ሴት የወለዱ ግን በሰማኒያ ቀን ነውና:: ይህን ሥርዓት መድኃኒታችንም ፈጽሟል:: በኦሪት እንደተጻፈ /ዘጸ.13÷2/ ምንም እንኳ እመቤታችን ጌታን ከመውለዷ በፊት ፣ በወለደችው ጊዜ፣ ከወለደችውም በኋላ ልማደ አንስት /ሕርስ/ እንዳልነበረባት ቢታወቅም /ቅድመ ጸኒስ ጊዜ ጸኒስ ድኅረ ጸኒስ፣ ቅድመ ወሊድ ጊዜ ወሊድ ድኅረ ወሊድ ንጽሕት ናትና::/ በኦሪት የተጻፈውን ለማክበር በወለደች ባርባ ቀኗ ሀብታሞች ሙክት እየሳቡ ሲሄዱ እሷም እንደ ድህነቷ ሁለት የወፍ ጫጩት /እጓለ ርግብ ዘውገ ማዕነቅ/ ይዛለት ወደ ቤተመቅደስ ወስዳዋለች /ሉቃ2÷22/ ይህ በብሉይ ኪዳን የነበረው ሥርዓት ባርባ ቀን በሰማንያ ቀን ለሚደረገው የክርስቲያን ልጆች ጥምቀት ምሳሌ ነው:: ሕፃናቱ ወደ እግዚአብሔር ፊት መቅረብ የሚጀምሩት በዚህ ቀን ነውና::

የሥርዓቱ አፈጻጸም እንደሚከተለው ነው:: ወላጆቹ የሚጠመቀውን ሕፃን ይዘው ወደ ቤተክርስቲያን ይመጣሉ:: ቄሱ ውኃውን በብርት አድርጎ ሥርዓተ ጸሎቱን ይጀምራል:: ክርስትና አባት እና እናት ለመሆን የመጡት የሕፃኑን አውራ ጣት ይዘው ተጠማቂው ሊለው የሚገባውን ሦስት ጊዜ «እክህደከ ሰይጣን» እያሉ ሰይጣንን ያወግዛሉ :: ሥርዓተ ጸሎቱ ተገባዶ ዲያቆኑ «ጸልዩ በእንተ ዛቲ ቤተክርስቲያን» ሲል ተጠማቂው ካደገ ከተማረ በኋላ የመጣ እንደሆነ ራሱ፣ ሕፃን ከሆነ ግን የክርስትና አባት/ እናት ጸሎተ ሃይማኖትን ይደግማሉ:: ይህ ሲፈጸም የተጠማቂው ልብስ ይወልቃል:: ዲያቆኑ በሁለት እጁ ተቀብሎ ተጠማቂው ሕፃን እንደሆነ በሁለት እጁ ይይዘዋል አዋቂ እንደሆነ ግን ራሱን የቻለ ስለሆነ ዲያቆኑ ይመራዋል እንጂ አይታቀፈውም፣ ማጥመቂያውን በአራቱ ማዕዘን እያዞረ በምሥራቅ በምዕራብ በሰሜን በደቡብ «እሰግድ ለአብ፣ እሰግድ ለወልድ፣ እሰግድ፣ ለመንፈስ ቅዱስ፣ ይላል» ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ እሰግዳለሁ ማለት ነው:: በዚህ ጊዜ ቄሱ በተጠማቂው ግንባር መስቀሉን እያደረገ «ይኩን ስመከ እገሌ» ይላል:: በክርስትና ስም ይሰይመዋል:: ይህ ሲፈጸም ማዩን «ቡሩክ» ብሎ ባርኮ

«አሐዱ አብ ቅዱስ አሐዱ ወልድ ቅዱስ አሐዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ፣» ካለ በኋላ «አጠምቀከ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ» እያለ ሦስት ጊዜ ብቅ ጥልቅ አድርጎ ያጠምቀዋል:: ምሳሌው እንዳለፈው ነው::

## የክርስትና ስም አወጣጥ፣

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ልዩ መልክ አለው:: ተጠማቂው የክርስትና ስም የሚወጣለት ቄሱ በሚያውቀው የዕለቱን በዓል ምክንያት አድርጎ ነው:: ለምሣሌ በዓሉ የጌታ የእመቤታችን የሆነ እንደሆነ ገብረ መድኅን፣ ኃ/ማርያም፣ የቅዱስ፣ የመልአክ እንደሆነ ኃይለ ጊዮርጊስ ወልደ ሚካኤል በሚል ስም ይሰይመዋል::

ስለ ስም ካነሣን በኢትዮጵያ ሁለት ዓይነት ስም አለ ወይም ለአንድ ሰው ሁለት ስም አለው:: ይኸውም አንዱ በጥምቀት በቤተክርስቲያን የሚወጣለት ነው:: ሌላው ግን ከቤተሰብ የሚወጣለት ነው:: ያኛውን የክርስትና ስም ይኸኛውን የዓለም ስም ይሉታል:: በብዙ የኢትዮጵያ ክፍሎች ለምሳሌ በሰሜን ሸዋ በትግሬና በኤርትራ ያሉት ክርስቲያኖች ብዙዎቹ የሚጠሩት በክርስትና ስማቸው ነው:: በዓለም ስማቸው የሚጠሩት ክርስቲያኖች በቤተክርስቲያን አገልግሎት በሚፈጸምላቸው ጊዜ ብቻ /በተክሊል ሲጋቡ፣ ሲታመሙ ለጸሎት፣ ሲሞቱ ለጸሎተ ፍትሐት/ ካልሆነ በቀር በክርስትና ስማቸው አይጠሩበትም:: ብዙዎቹ የክርስትና ስማቸው እንዳይጠፋባቸው በውቅራት ከሰውነታቸው ላይ ያስከትቡታል:: በማይታወቁበት ቦታ በድንገት ሲሞቱ ያለ ጸሎተ ፍትሐት እንዳይቀበሩ ለጥንቃቄ ነው:: ዛሬ ግን የጥምቀት መዝገብ ስላለና የምስክር ወረቀትም ስለሚሰጥ ችግር የለም:: ይህ በዓለም ስም መጠራት የተጀመረው መቼ እንደሆነ በትክክል ባይታወቅም፣ የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ተደጋግሞ መከራ የደረሰባቸው ስለሆነ ክርስቲያኖችን የሚያሳድድ ጠላት በመጣ ቁጥር የክርስትና ስማቸውን እየደበቁ ለመዳን የፈጠሩት ዘዴ ሳይሆን አይቀርም፣ እንደ ኢትዮጵያ ክርስቲያኖች በዓረብ አገር የሚኖሩ ክርስቲያኖችም ብዙዎቹ እንደዚሁ በዓለም ስማቸው ይጠራሉ:: ምክንያቱ ተመሳሳይ ነው:: እንደ አጋጣሚ ሆኖ ተለምዶ ቢቆይም፣ በቅድስት ቤተክርስቲያን አደባባይ የተሰጠው የክርስትና ስም ተደብቆ በሌላ ስም መጠራት ክርስቲያናዊ ትውፊት አለመሆኑን ካህናትም ምእመናንም ተረድተው ወደ ክርስትና ስማቸው ቢመለሱ መልካም ነው:: ስያሜውና ጥምቀቱ ሲያበቃ ለክርስትና አባት፣ እናት ያስረክባል:: ከልጅህ/ሽ/ የማትለየው በክርስቲያናዊ ምግባርና ሃይማኖት የምታሳድገው የቋል ኪዳን ልጅህ ነው እያለ፤ እሱም እሺ አዎ እያለ ይቀበላል:: በዚህ ጊዜ ሜሮን ይቀባል:: ሦስት ኅብረ ቀለማት ያሉት ፈትል ተገምዶ በአንገቱ ይታሠርለታል፣ ይህም በግእዝ «ማኅተም» በአማርኛ ግን «ማተብ» ይባላል:: ቀለሙ ሦስት ዓይነት ነው:: ነጭ፣ ቀይና ቢጫ:: ነጩ የአብ ምሳሌ ነው ቀዩ የወልድን ሥጋ መልበስ፣ ቢጫው የመንፈስ ቅዱስ፣ የቤተክርስቲያን ተስፋ መንፈስ ቅዱስ ነውና:: ሦስት መሆኑ የምሥጢረ

ሥላሴ፣ አንድ ሆኖ መገመዱ የአንድ አምላክ ምሳሌ ነው:: ዛሬ ግን አንዳንዶቹ በፈትሉ ፈንታ ባለወርቅ መስቀል ሀብል ያሥሩባቸዋል:: መስቀሉ ባይከፋም ሀብሉ ለምሳሌነት አይመችም:: ሕፃኑ ልብሱን ከመልበሱ በፊት ቄሱ ሕፃኑን እንደገና ተቀብሎ በሁለት እጁ ከፍ አድርጐ ይዞ «ይባዕ መንፈስ ቅዱስ» እያለ እፍ ይልበታል:: ከዚህ በኋላ ተጠማቂው ወደ ቤተክርስቲያን ገብቶ ይቆርባል:: የጥምቀት ሥርዓት የሚፈጸመው ተጠማቂው ሲቆርብ ነውና:: እዚህ ድረስ የቤተክርስቲያናችን ሥርዓተ ጥምቀት አፈጻጸም ነው::

ይህ የእኛ ሥርዓት ከሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ጋር የማይመሳሰልበትም የውጭ መልክ አለው:: እዚህ ላይ በመጠኑም ቢሆን አንዳንድ ምልክቶችን እናቀርባለን:: በመጀመሪያ «የሕፃናት ጥምቀት» እስታሊን በሚባለው የስዊዘርላንድ ክፍለ ሀገር አባካሊ በምትባል ከተማ በሚገኘው የፕሮቴስታንት ቤተክርስቲያን ሕፃን ልጅ ሲጠመቅ አይቼአለሁ:: ሌሎችም የፕሮቴስታንት ተከታዮች በጀርመንም እንደሚያጠምቁ ነግረውኛል:: ከላይ እንዳየነው ከፕሮቴስታንት ማኅበር በቀር ሐዋርያዊ ውርስ ባላቸው አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ይሠራበታል:: ቀን ግን አይወሰንም፣ እንደመጣ ነው፣ በምሥራቃውያን አብያተ ክርስቲያናት በተለይ እንደኛ የተለመደ የማጥመቂያ ጊዜ አድርገው ባይወስዱትም፣ ወንድ የወለዱ ባርባ ቀን ሴት የወለዱ በሰማኒያ ቀን ወደ ቤተክርስቲያን እየሄዱ ልዩ ጸሎት ይደረግላቸዋል:: በየጊዜው እየለዋወጡ ትና እየረሱት ነው እንጂ ይህ ጸሎት የክርስትና ሥርዓት ይፈጸምበት የነበረ ሳይሆን አይቀርም:: ስም አወጣጡም በጣም የተለየ ነው:: አብዛኛውን ጊዜ ምሥራቃውያንም ሆኑ ምዕራባውያን ስም የሚሰይሙት፣ የጌታን፣ የእመቤታችንን የቅዱሳንንም ሆነ የመላእክትን ስም እንዳለ ወስደው ነው:: ለምሳሌ፣ «አማኑኤል፣ ማርያም፣ ጴጥሮስ፣ ጊዮርጊስ፣ ሚካኤል» እያሉ ነው:: ካቶሊኮች ሁለቱንም ስም ነው የሚሰይሙት፣ ስም የሚወጣው ከአያት ከቅድመ አያት ስም እየተወሰደ ነው:: ፕሮቴስታንቶችም ጀምረዋል:: የክርስትና እናት አባት አላቸው:: ሀብልም ያሥራሉ:: በግሪኮችና በሌሎችም መለካውያን ሥርዓት ቄሱ ተጠማቂውን ወደ ማጥመቂያው ሲዘፍቀው «ይጠመቅ ገብረ እግዚአብሔር በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ» እያለ ነው:: ለዚህም የሚሰጡት ምክንያቶች መሣሪያዎች ነን እንጂ አጥማቂዎች አይደለንም አጥማቂው እግዚአብሔር ነው ይላሉ:: አሳባቸው የትሕትና ይመስላል፣ ነገር ግን «<u>አጠምቀከ</u> የሚለው ገቢር ቃል «ወእንዘ <u>ታጠምቅዎም</u>» ከሚለው ትእዛዝ ጋር የተስማማ ነው፣ በትእዛዙ ውስጥ ሐዋርያትም ባድራጊነት አሉበት:: ምዕራባውያንም «አጠምቀከ» ይላሉ:: በኢትዮጵያና በግብጽ ሥርዓትም እንደዚሁ በገቢር ነው:: «አጥመቀ» ካለው ነጠላ ቀጥር ሌላ በአንዳንድ መጻሕፍት ቀጥሩን አብዝቶ «ናጠምቀከሙ ብሎ ይገኛል» የአቡሊዲስ ቀኖና እና «ዲድ7» በማጥመቂያው ሦስት ጊዜ ብቅ ጥልቅ አድርጎ ማውጣት በሁሉም አብያተ ክርስቲያናት ይሠራበታል:: በችግር ካልሆነ በቀር በምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት /በመለካውያንም ቢሆን/ ጥምቀት በንዝኅት አይሆንም:: በምዕራብ አብያተ ክርስቲያናት ግን ሁልጊዜ

በንዝኅት ነው፡፡ ከጥምቀትና ከሜሮን በማከታተል የሚፈጸመውም ምሥጢረ ቁርባን በሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ጨርሶ ተረስቶ በኢትዮጵያ ብቻ ይሠራበታል፤ ምዕራባውያን አጥምቀው ያለ ሜሮንና ያለ ቁርባን ያሰናብታሉ፡፡ መለካውያንም አጥምቀው ሜሮን ቀብተው ሳያቆርቡ ይለያያሉ፣ የሚያቆርቡት ሰንብተው ነው፣ የሚሰጡትም ምክንያት በአንድ ቤተክርስቲያን ያላቸው ካህን አንድ ስለሆነ አጥምቆ ወዲያውኑ ሥርዓተ ቁርባንን ለመፈጸም የማይችል በመሆኑ ብቻ ነው፡፡ ችግር ባለበት /በሕንድም/ እንደዚሁ ይሠራሉ፡፡ ይህንን ጄኔቫ በሚገኘው የራሽያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያንም አይቼአለሁ፡፡ ሁሉም የጥምቀትን ሥርዓት የሚፈጽሙት ከቅዳሴ በኋላ በሰርክ ነው፡፡ በመጠኑም እስከዚህ ያየነው የጥምቀት ምሥጢርና አፈጻጸሙ ነው፡፡

## 2. ምሥጢረ ሜሮን፣

«ሜሮን» ቃሉ የጽርዕ ነው፣ የሚሸት የሚጣፍጥ፣ ልብ የሚመስጥ መዓዛ አለው፡፡ መልኩ ጽርየቱ ዘይት የሚመስል ነው፡፡ «ሜሮዲያ» ይላል÷ በግሪክ መዓዛ ማለት ነው፡፡ በግእዝም ቅብዕ፣ ቅብዐ ሜሮን ይባላል÷ ከብዙ ዕጽዋት ተቀምሞ የሚሠራ ነው፡፡

ጥቅሙና አገልግሎቱ በብሉይ ኪዳን ለእግዚአብሔር የሆነው ሁሉ የሚታተምበት ያደፈው የረከሰው የሚቀደስበት ቅብዕ ነው፡፡ እግዚአብሔርን ለማገልገል የሚሾሙ ሊቃውንትና ካህናት አራት ሽቱ አምስተኛ ዘይት/ የሚቀቡት ቅብዕ ይህ ነበር፡፡ የእግዚአብሔርን ሕዝብ እሥራኤልን የሚጠብቁ የእግዚአብሔር እንደራሴዎች ነገሥታትም «መሲን» የሚባሉት በዚህ ተቀብተው ስለሚነግሡ ነው፡፡ «መሲሕ» ማለት ቅቡዕ የተቀባ ማለት ነውና፡፡ /ዘፍ.20÷23–33፡፡/ ቀዳ.ሳሙ.10÷1፡፡ 16÷12–13፡፡ ይህም ብቻ አይደለም፣ እግዚአብሔር የሚገለገልባቸው የቤተመቅደስ ንዋያትም አስቀድመው በዚህ መቀባት መታተም ነበረባቸው፡፡ ከተቀቡም በኋላ ለቤተመቅደስ እንጂ ለተራ አገልግሎት አይውሉም ነበር፡፡ ከብሉይ ኪዳን በፊት የነበረው አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር ያደረገው ከአሥሩ አበው አንዱ ሄኖክ ከመሰወሩ በፊት ሜሮን ተቀብቶ እንደ ተሰወረና ልማደ ሰብእ እንደጠፋለት ይነገራል፡፡ /ራዕይ. 11÷4/ ነገርን ነገር ያነሣዋልና ከዚህ ላይ አነሳነው እንጂ በምሳሌነት ሲሠራበት የኖረው ይህ የነርሱ ቅብዕ በቤተክርስቲያን ላለው ቅብዐ ሜሮን ጓዱ ዘመዱ አይደለም፡፡ የቤተክርስቲያኑንስ እንደሚከተለው እንመልከት፡፡

በሐዋርያት ጊዜ ማንኛውም አማኝ ከተጠመቀ በኋላ የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ የሚቀበለው በሐዋርያት አንብሮተ እድ ማለት ሐዋርያት እጃቸውን ሲጭኑበት እንደነበርና ከሐዋርያት በኋላ የተነሡ ኤጲስ ቆጶሳትም ይህንኑ ሲሠሩበት መቆየታቸውን ስለ ምሥጢረ ጥምቀት በተናገርንበት አንቀጽ አንሥተነው ነበር፡፡ የምእመናን ቁጥር ሲበረክት ኤጲስ ቆጶሳትም በየቦታው በቅርብ ስለማይገኙ የቤተክርስቲያንን የመግቦት ተልእኮ ለማፋጠን ሲባል፣ ኤጲስ ቆጶሳት ሜሮን እያፈሉ በሜሮኑ ላይ

እየቀደሱ ወደአብያተ ክርስቲያናት እንዲልኩና የሚጠመቁ ምእመናንም በእነሱ አንብሮተ እድ ፈንታ ሜሮን እንዲቀቡ በሉድቅያ ጉባኤ ተወሰነ:: /ጉባኤ ሉድቅያ ቀኖና 48/ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ አማኞች ተጠምቀው ከማጥመቂያው ሲወጡ ያጠመ ቃቸው ቄስ ሜሮን ይቀባቸዋል:: በአንብሮተ እድ ፈንታ ሜሮን እንዲተካ ሥርዓት የተሠራው ቅዱሳት መጻሕፍትን መሠረት በማድረግ ነው::

ቅብዐ ሜሮን በብሉይ ኪዳን በምሳሌነት ይሠራበት ከነበረው ሌላ አዲስ ኪዳንን የጻፉት ቅዱሳን ሰዎችም የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ ቅብዐት ይሉት ነበር:: /ቆሮ ካልእ.1÷21፣ ቀዳ.ዮሐ.2÷20/ ቅብዕን የመንፈስ ቅዱስ ማኅተም ይሉታል:: /ኤፌ.1÷13፣ 4÷30/ ማኅተም ያለበት ሁሉ ማንነቱ እንደሚታወቅ ምእመናንም የመንፈስ ቅዱስ ገንዘቦች መሆናቸው የሚታወቀው /የሚረጋገጠው/ በጥምቀት በቅብዐተ ሜሮን ሲታተሙ ነውና::

የምእመናን ሁለተኛ ልደት ከውኃና ከመንፈስ ስለሆነ ምእመናን በውኃ ሲጠመቁ÷ ሜሮን ሲቀቡ፣ ከመንፈስ ቅዱስ ይወለዳሉ:: /ዮሐ.3÷5/ ስለሜሮን አወጣጥ /አፈላል/ በጥንታዊት ቤተክርስቲያን ትውፊት እንደሚታወቀው ጌታ ከተገረፈባቸውና ከተሰቀለባቸው ዕጽዋት ተሰብስቦ የተነጠረ ነው:: ከተነጠረ በኋላ ኤጲስ ቆጶሳት ተሰብስበው ምሕላና ጸሎት ያደርሱበታል ይቀድሱበታል:: ኋላም በአንብሮተ እድ ባርከው ወደየሀገረ ስብከታቸው ያከፋፍሉታል:: የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ለብዙ ዓመታት ሜሮን የሚመጣላት ከእስክንድርያ ቤተክርስቲያን ነበር:: አሁን ነፃነቷን ካገኘች በኋላ ግን ፍልሀተ ሜሮ" አስፈላጊ ሲሆን ስለ መንበረ ማርቆስ ክብር የኢትዮጵያ ጳጳሳት ወደ ካይር እየተላኩ ከግብጽ ጳጳሳት ጋር ሆነው የፍልሀተ ሜሮንን ሥርዓት ይፈጽማሉ:: የኢትዮጵያንም ድርሻ ተካፍለው ያመጣሉ:: በግብጽ የሚደረገው ፍልሀተ ሜሮን ሁልጊዜ በሰኔ ወር ነው:: መጀመሪያው ፍልሀተ ሜሮን ተደረገ የሚባለው በሰኔ ስምንት ቀን ነውና:: /ስንክሳር ሰኔ 8/ በመለካውያን ዘመን ሜሮን የሚፈላው የጸሎተ ሐሙስ ዕለት በቅዳሴ ላይ ነው:: ግሪኮች የቆስጥንጥንያን መንበር ለማክበር ሲሉ ጳጳሶቻቸውን ወደ ቁስጥንጥንያ ልከው በዚያ ፍልሀተ ሜሮን ያደርጋሉ:: ሌሎች መለካውያን ግን በየቦታቸው ነው:: የሮማ ካቶሊክ ቤተክርስቲያንም የሜሮንን ምሥጢርነት ትቀበላለች:: አፈጻጸሙ ግን እስከአሁን ካየነው የተለየ ነው::

## የሜሮን አቀባብ

በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት ከላይ እንደገለጥነው የሜሮን አቀባብ ወዲያው ከጥምቀት አያይዞ ይፈጸማል፣ አቀባቡ እንደዚህ ነው:: የተጠመቀው ሕፃን እንደሆነ ከመጠመቂያው ወጥቶ እንደቆመ፣ ቄሱ ሜሮኑን በአውራ ጣቱ እየጨለፈ «እቀብአከ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ» እያለ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም በትእምርተ

መስቀል ያትመዋል:: በመጀመሪያ ግንባሩን ያትመዋል፣ አእምሮው የተባረከ እንዲሆን:: ግራና ቀኝ ዓይኖቹን ያትመዋል፣ ዓይኖቹ የእግዚአብሔርን እውነት እንዲያዩ:: ግራ ቀኝ ጆሮዎቹን ያትመዋል፣ ጆሮዎቹ የእግዚአብሔርን ቃል እንዲሰሙ:: አፉን ከናፍሩን ያትመዋል፣ እውነት እንዲናገር÷ የእግዚአብሔርን ጥበብ እንዲማር:: ደረቱን ያትመዋል፣ በልቡ ቅን እንዲሆን እንዲያስብ:: ግራ ቀኝ እጆቹን ይቀባዋል፣ በጎ እንዲሠራባቸው:: ግራና ቀኝ እግሮቹን ይቀባቸዋል፣ ወደ መልካም ሥራ እንዲፋጠኑ:: ባጠቃላይም መላ ሰውነቱን ይቀባዋል፣ መላ ሰውነቱ የእግዚአብሔር ማደሪያ እንዲሆን::

በሜሮን የሚታተሙ በሜሮን የሚቀደሱ አዲስ ክርስቲያኖች ብቻ አይደሉም:: አዲስ ቤተክርስቲያን ተሠርቶ ካለቀ በኋላ አገልግሎት የሚጀመርበት በሜሮን ከተቀባና ከከበረ በኋላ ነው:: የቤተክርስቲያን የውስጥ ንዋያት፣ ታቦት፣ ጻሕል፣ ጽዋ፣ ዕርፈ መስቀል፣ መሶበ ወርቅ፣ ማዕጠንት፣ ማኅፈድ፣ መንበር እነዚህን የመሳሰሉትም ለአገልግሎት ከመቅረባቸው በፊት በሜሮን ይታተማሉ:: ልዩ ጸሎትና ቡራኬም ይፈጸምባቸዋል:: ከዚያ በኋላ ተራ ሥራ አይሠራባቸውም:: በግሪክና በሌሎቹ መለካውያን አቀባቡ ከእኛው ጋር ተመሳሳይነት አለው:: ከጥምቀት ጋር አያይዘው ይቀባሉ:: ሲቀቡ ግን «ማኅተም ጸጋ ዘመንፈስ ቅዱስ ዝ ውእቱ» እያሉ ነው:: የሚቀባው ቄሱ ነው:: በሮማ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን በፊት እንደተናገርነው ምሥጢረ ሜሮን የሚፈጸመው ሕፃኑ ተጠምቆ አሥር ዓመታት ያህል ከቆየ በኋላ ነው:: /Confirmation ይሉታል/ የሚቀባው ኤጴስ ቆጶሱ ብቻ ነው:: ቄስ የመቀባት መብት የለውም:: ፕሮቴስታንቶች ግን የሜሮንን ምሥጢርነት አይቀበሉም::

## 3. ምሥጢረ ቁርባን

ቁርባን የሱርስት ቃል ነው:: መባዕ ስጦታ አምኃ ማለት ነው:: ሥጋውና ደሙ የተሰጠን በነጻ ያለ ዋጋ ሳይገባን በችሮታ ነውና፣ ቁርባን ይባላል:: ጽርዓውያንም «አምላካዊት ሱታፌ» «አምላካዊት ደስታ» ይሉታል:: ምእመናን ከአባታቸው ከእግዚአብሔር ተገናኝተው ደስ የሚላቸው የክርስቶስን ሥጋና ደም ሲቀበሉ ነውና:: ሥጋውና ደሙ የሚሠራው ከስንዴና ከወይን ነው:: ምሥጢረ ቁርባንን የመሠረተው ራሱ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: «ከሰማይ የወረደ ኅብስት እኔ ነኝ:: ሥጋዬን የበላ ደሜን የጠጣ የዘለዓለም ሕይወት አለው» እያለ ያስተማረውን /ዮሐ.6÷32-63/ ተማሪዎቹ በምር እንዲረዱት የጸሎተ ሐሙስ ዕለት ማታ ለበረከት ከመጣለት ኅብስት ያላረረውን ያልጠቆረውን ነቅዕ ነጭ የሌለውን አንሥቶ ባርኮ ፈትቶ አቀጣጥኖ «ነገ ለእናንተ በመልዕልተ መስቀል የሚቆረሰው ሥጋዬ ይህ ነው እንኩ» ብሎ ሰጣቸው:: ወይኑንም እንደዚሁ ባርኮ «ነገ ስለእናንተ በመልዕልተ መስቀል የሚፈሰው ደሜ ይህ ነው እንኩ ጠጡ» ብሎ ሰጣቸው:: ይህን ከሰጣቸው በኋላ እነሱም ሞቱን እያስታወሱ ሁልጊዜ ይህን እንዲያደርጉ አዟቸዋል:: /ማቴ.26÷26-28:: ማር.14÷22-24:: ሉ ቃ22÷19-20/

የክርስቶስ መሥዋዕትነት በብሉይ ኪዳን ለአያሌ ዓመታት በትንቢት በምሳሌ ሲነገር የኖረ ነው። «ደሙ ምልክት ይሁንላችሁ» ዘጸ.12÷13፣ ተብሎ እንደተነገረ እሥራኤል ሥጋውን በልተው ደሙን ረጭተው በግብጽ ከወረደው መቅሰፍት /ዘጠኝ መቅሰፍት አሥረኛ ሞተ በኩር/ የዳኑበት በግ የመሲሕ መሥዋዕትነት ምሳሌ ነው። ነቢያት እነ ኢሳይያስ እነ ኤርምያስም ለትንቢታቸው ርዕስ ያደረጉት የመሲሕን መሥዋዕትነት ነው። /ኢሳ.53÷7/ ኤር.11÷19/ ከዚህ ሁሉ የሚቀድም ደግሞ በኦሪት ዘፍጥረት እንደተገለጠው መልከ ጸዴቅ ለአብርሃም መስተንግዶ ያቀረበው ኅብስትና ወይን የክርስቶስ ሥጋና ደም ምሳሌ ሁኗል። ዘፍጥ.14÷18–19/ የሐዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች ቅዱሳን ሐዋርያትም ስለ ክርስቶስ መሥዋዕትነት በተናገሩበት አንቀጽ ሁሉ በግብጽ የታረደው በግ ምሳሌ አድርገው እየጠቀሱ ነው። /ቀዳ.ጴጥ.1÷19/ ይሁ.1÷29–36። ራእይ.5÷6–12/ ከዚህም ሌላ እሥራኤል በምድረ በዳ ሳሉ በተአምራት ከሰማይ እየወረደላቸው አርባ ዓመት ሙሉ የተመገቡት መና ምንም እንኳ ከሞት ባያድን በተአምራት በመገኘቱ ለሥጋውና ለደሙ ምሳሌ ሆኗል። /ዮሐ.6÷49/

ቅዱሳት ሐዋርያት በማስተማር ዘመናቸው ሁሉ ምሥጢረ ቁርባንን ይፈጽሙ ነበር። ነገር ግን እንደዚህ እንደ አሁኑ ቤተክርስቲያን ነጻነቷን አግኝታ እንደምታደርገው በይፋ ሳይሆን በምእመናን ቤት ነበር። ቅዱስ ሉቃስ በሐዋርያት ሥራ እንደገለጠው ሁልጊዜ ከማስተማርና ከጸሎት ጋር ምሥጢረ ቁርባንም ነበር። /የሐዋ. 20÷27። 2÷42/ ተማሪው ቅዱስ ሉቃስ በሐዋርያት ሥራ «ፈትቶ ኅብስት» እያለ በተራ ቃል የተገለጠውን መምህሩ ቅዱስ ጳውሎስ «የጌታ ማዕድ የጌታ ጽዋ» /ቀዳ.ቆሮ.10÷2/ እንዲያውም «የጌታ ሥጋና ደም» እያለ ገልጦ ያስተምር ነበር። /ቀዳ.ቆሮ.11÷27/

በዘመነ ሰማዕታት የነበሩ ክርስቲያኖችም ማለት እስከ አራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ የነበሩት ክርስቲያኖች በየተሰደዱበት ቦታ በዋሻ በፍርኩታ ውስጥ /ካታኮምብ/ ምሥጢረ ቁርባንን ይፈጽሙ ነበር። ከዚህም የተነሣ ባላመኑ አረማውያን ዘንድ «ክርስቲያኖች ሰው ይበላሉ» እየተባሉ ይወነጀሉ እንደነበር በቤተክርስቲያን ታሪክ ተመዝግቧል።

ምንም ቢሆን «ንዜኑ ሞተከ ወትንሣኤከ፤ ሞትህንና ትንሣኤህን አንረሳም ሕይወታችን ነውና ዳግም ምጽአትህንም በናፍቆት እንጠባበቃለን» እያሉ ክርስቲያኖች የክርስቶስን መከራ በቅዳሴ ጊዜ ይዘምሩታል። ከሕይወታቸውም ፍጻሜ በኋላ ስለሚወርሱት ሕይወት ያላቸውን ተስፋ በናፍቆት የሚጠባበቁ መሆናቸውን ይገልጣሉ።

ምሥጢረ ቁርባን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የጌታ የሐዋርያትን ከዚያም የቤተክርስቲያን አባቶች ያቆዩትን ሥርዓት መሠረት በማድረግ ይፈጸማል።

መሥዋዕቱ የሚዘጋጀው በቤተክርስቲያኑ ቅጽር ውስጥ በስተምሥራቅ በኩል በሚገኘው ቤት ነው። ይህ ቤት «ቤተልሔም»

ይባላል:: ክርስቶስ በተወለደባት ከተማ በቤተልሔም የተሰየመ ነው:: የክርስቶስ የማዳን ሥራው ከቤተልሔም እስከ ቀራንዮ ነው:: ቤተክርስቲያን ቀራንዮ ናት:: መሥዋዕትን የሚያዘጋጁት ዲያቆናት ናቸው:: በቤተልሔም መሥዋዕቱ ሲዘጋጅ ቄሱ በቤተመቅደስ የመግቢያ ጸሎት እያደረገ ይቆያል:: በቤተመቅደስ ባሉ በንዋያተ ቅድሳት ላይም ለእያንዳንዳቸው የታዘዘውን ቡራኬና ጸሎት ያደርሳል:: ልብሰ ተክህኖውን ከመልበሱ በፊት በክንዱ ይዞ ይጸልያል:: ጸሎቱን ሲጨርስ ኤጲስ ቆጶሱ ያለዚያም በዕድሜ የሚበልጠው በሹመት የሚቀድመው ቄስ ባርኮለት ሁሉም ካልተገኙ ራሱ ባርኮ ይለብሳል:: ከዚህ በማያያዝ በንዋያቱ ላይ በየተራ የቡራኬ ጸሎት ይጸልያል በቤተመቅደስ የሚገኙ ነዋያት ከታቦቱ ሌላ የሚከተሉት ናቸው::

ሀ. መሶበ ወርቅ- መሥዋዕቱ ከቤተልሔም የሚመጣበት ነው::

ለ. ጽዋ- የደሙ መያዣ፣

ሐ. ፃሕል- የሥጋው መያዣ

መ. አውድ- ምእመናንን ለማቁረብ ሥጋውን የሚይዙበት

ሠ. ዕርፈ መስቀል- ደሙን የሚያቀብሉበት፣

ረ. ጽንሐሕ - ማዕጠንት የሚታጠንበት

ሰ. ሙዳይ-የዕጣን ማስቀመጫ

ሸ. ማኅፈድ- በጻሕሉ ላይ የሚነጠፍና ሥጋው የሚሸፈንበት::

እነዚህ ንዋያት በየተራ ይባረካሉ:: በመጀመሪያ ለቤተመቅደስ አገልግሎት የሚውሉት ሜሮን ተቀብተው ተባርከው ነው:: በቅዳሴም ጊዜ ለያንዳንዳቸው የቡራኬ ጸሎት አላቸው::

የቤተልሔሙ ዝግጅት ሲያበቃ ቅዳሴውን የሚሳተፉት ዲያቆናትና ቀሳውስት እያስባረኩ ልብሰ ተክህኗቸውን ይለብሳሉ:: ተንበርክከው ጸሎት ያቀርባሉ:: ከዚህ በኋላ ፍሬ ሰሞነኛው ዲያቆን መሶበ ወርቁን ግምጃ አልብሶ በራሱ ተሸክሞ /አክብሮ/፣ ንፍቁ፣ /ተራዳኢው/ ቄስ ሻኩራውን ይዞ ከኋላ እያጠነ መሥዋዕቱን ለማምጣት ወደ ቤተልሔም ይወርዳሉ:: ሠራዒው ዲያቆን ክቡር ደሙ የሚሆነውን መሥዋዕት ይዞ ቅዱስ ሥጋው የሚሆነውን መሥዋዕት በመሶበ ወርቁ ይዞ ቃጭሉን እያ ቃጨለ ንፍቁ ቄስ ማዕጠንቱን እያሳረገ ወደ ቤተክርስቲያን ይገባሉ:: በዚህን ጊዜ ቅዳሴ መጀመሩን የሚያውጅ ደወል ይደወላል:: በዚህ ጊዜ ሠራዒው ቄስ ተገቢውን ምንባብ እያነበበ እጆቹን ያነጻል:: ይታጠባል- እጆቹን በመሶበ ወርቁ ላይ አመላክቶ መንበሩን ይዞራል:: ኤጲስ ቆጶስ ካለ መሥዋዕቱን ባርኮ ይሰጠዋል፤ ያለዚያም ራሱ ቅዳሴውን ይጀምራል:: ስለ ጸሎተ ቅዳሴው ተራ በመጽሐፈ ቅዳሴ ተጽፏል:: በቅዳሴ ጊዜ የሚነበቡ መጻሕፍት የሚከተሉት ናቸው::

ሀ. ከጳውሎስ መልእክታት- ሠራዒ ዲያቆን፣

ለ. ከሰባቱ መልእክታት -ንፍቅ ዲያቆን

ሐ. ከግብረ ሐዋርያት- ንፍቅ ቄስ

መ. ምስባክ ከዳዊት መዝሙር –ሠራዒ ዲያቆን
ሠ. ከወንጌላት– ሠራዒ ቄስ

«ጳኡ ንዑሰ ክርስቲያን» የሚባለውና ደወል የሚመታው ወንጌል ከተነበበ በኋላ ነው:: የክርስትናን ትምህርት በመማር ላይ ያሉ ንዑስ ክርስቲያን ወንጌል እስኪነበብ ድረስ በቤተክርስቲያን አገልግሎቱን ይከታተላሉ:: ከወንጌል በኋላ ግን ይወጡ ነበር:: አሁን ግን ንዑስ ክርስቲያን ቢኖሩም ባይኖሩም ዲያቆኑ «ፃኡ ንዑስ ክርስቲያን» ብሎ ቃጭሉንም ደወሉንም ያስተጋባዋል:: እስከዚህ ያለው የቅዳሴ ክፍል የሥርዓትና የትምህርት ክፍል ነው:: ከዚህ በኋላ ፍሬ ቅዳሴ ይጀመራል:: ቄሱ «ሀበነ» ሲል መሥዋዕቱ ይለወጣል:: «ይወርድ መንፈስ ቅዱስ በላዕለ ኅብስቱ ወወይኑ፣ ሶብ ይብል ካህን ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ፊኑ» /መልክዐ ቁርባን ተመልከት/ ድርገት ከመውረዳቸው በፊት አርባ አንድ ጊዜ «እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ» ተብሎ፣ በውጭ ሃይማኖተ አበው ይነበባል:: በውስጥም ቄሱ ስለ ሥጋውና ደሙ ሦስት ጊዜ የምስክርነት ቃሉን ይሰጣል:: የምስክርነት ቃሉ፣

1. ይህን ሥጋና ደም የእግዚአብሔር ልጅ ቅድስት ንጽሕት ከምትሆን ከእመቤታችን ድንግል ማርያም የነሣው መሆኑን አምናለሁ:: ያለ መቀላቀል፣ ያለ መለያየት፣ ያለመለወጥ፣ አንድ አካል አንድ ባሕርይ የሆነ በጰንጤናዊው በጲላጦስ ፊት እውነትን የመሰከረ፣
2. መለኮት ከትስብእት አለመለየቱን አምናለሁ:: አንድ ሰዓትም ቢሆን ለዓይን ጥቅሻ ያህልም እንኳ አምነን ለምንቀበለው ሁሉ ለሕይወትና፣ ለመድኃኒት፣ ለኃጢአትም ስርየት ተሰጠን እንጂ፣
3. ከሰማያዊ የባሕርይ አባቱና ከሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ክብርና ምስጋና የሚገባው የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋውና ደሙ ይህ መሆኑን አምናለሁ:: ብሎ ይመሰክራል::

ይህ የምስክርነት ቃሉ «ተቀላቀለ ተጣፋ» የሚሉ እነ አውጣኪን፣ «ከተዋሐደ በኋላ አንድ አካል አንድ ባሕርይ አልሆነም» የሚሉ መለካውያንን፣ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ያሳነሱትን እነ አርዮስን ያወግዛል:: ከዚህ በኋላ የንስሐ ጸሎት ጸልዮ ይቆርባል:: አብረውት የቀደሱትንም ያቆርባቸዋል:: ድርገት ወርደው ምእመናንን በሚያቆርቡበት ጊዜ ቄሱ ሥጋውን ዲያቆኑ ደሙን ያቀብላል፣ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሥርዓተ ቅዳሴ ለመቀደስ አምስት ልዑካን ያስፈልጋሉ:: ሦስት ዲያቆናትና ሁለት ቄሶች፣ እነሱም አንድ ሠራዒ ቄስ፣ አንድ ንፍቅ ቄስ፣ አንድ ሠራዒ ዲያቆን፣ አንድ ንፍቅ ዲያቆን፣ አንድ አብሪ ናቸው:: በገዳማትና በታላላቅ አድባራት ግን ሰባት ልዑካን ካልተሟሉ አይቀደስም::

የቅዳሴው ሰዓት በጾም ወራት ከቀኑ በዘጠኝ ሰዓት ነው:: በበዓለ ሃምሳና ቅዳሜ በሠለስት፣ እሑድ በነግህ፣ በትንሣኤ፣ በልደትና በጥምቀት ግን በመንፈቀ ሌሊት ይቀደሳል:: ለሕዝብ አገልግሎት ተብሎ ነው እንጂ

በታላላቅ በታዎች ከትንሣኤ፣ ከበዓለ ሃምሳ፣ ከእሑድ ቅዳሜ ከልደትና ከጥምቀት በቀር ምን ጊዜም ቅዳሴ በዘጠኝ ሰዓት ነው:: አንዳንድ የላቲን ቤተክርስቲያን ጸሐፊዎች የእኛን ቤተክርስቲያን ሥርዓት ሲያናንቁ «የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን በዘጠኝ ሰዓት የምትቀድሰው ቁርባን ጾም ያሽራል ብላ ስለምታምን ነው» ይላሉ:: /Archdole A.King, The rites of Eastern Christondom 1947 p.572/ ነገር ግን ይህ ባለማወቅ ባለመጠየቅ በግምት በይሆናል የተሰጠ አስተያየት ነው:: በመሠረቱ ቁርባን መቀበል ማለት የክርስቶስን አማናዊ ሥጋ አማናዊ ደም መቀበል ማለት ነው:: የምንቀበለው የክርስቶስ ሥጋና ደም ነፍስ የተለየው መለኮት የተዋሐደው ነው:: የጌታም ቅድስት ነፍሱ ከቅድስት ሥጋው የተለየችው ወንጌላውያን እንደ መሰከሩት በዘጠኝ ሰዓት ነው:: /ማቴ.15÷34-37 ሉ ቋ23÷44-46/ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በሰዓት የምትቀድሰው ጌታ ለእኛ ብሎ የሞተበትን ሰዓት ለማስታወስ ነው:: «ይህን በምታደርጉበት ጊዜ የሞቴን መታሰቢያ ታደርጋላችሁ» ብሏልና በተወሰኑ ዕለታት በሠልስት፣ በነግህና በመንፈቀ ሌሊት የምትቀድሰውም ድርጊቶች የተፈጸመባቸውን ሰዓቶች ለማስታወስ ነው:: እውነቱ ይህ ሆኖ ሳለ አንዱ ክርስቲያን ነኝ ባይ በሌላው ክርስቲያን ላይ ያልሆነ ወሬ ጽፎ መበተን፣ የክርስቲያኖችን እውነተኛነት ያስጠረጥረዋል:: በሞት አፋፍ ላይ ያለ ሕመምተኛ ቀድሳችሁ አቁርቡኝ ቢል በማናቸውም ሰዓት ቀድሰው ያቆርቡታል:: ቀዳሾች ግን ዘጠኝ ሰዓት እስኪሆን ድረስ በመቅደስ ውስጥ ቆይተው በዘጠኝ ሰዓት ሠርሖተ ሕዝብ ያደርጋሉ:: ከቁርባን በኋላ የቀደሱት ካህናትና የቀረቡት ምእመናን እስከ በነጋው ድረስ እጅ እግርን መታጠብ መስገድ፣ መንበርከክ፣ መረቆት፣ ምራቅ መትፋት፣ ደም በጥቶ ማውጣት፣ ጥፍር መቁረጥ፣ ራስ መላጨት፣ የሚያደክም ጉዞ መጓዝ፣ ከሰው ጋር መጨቃጨቅ፣ ወሸባ መግባት፣ ከመጠን በላይ መብላት መጠጣት፣ ሥጋዊ ፈቃድን መፈጸም ይህንና ይህን የመሳሰሉትን ማድረግ ክልክል ነው:: /መጽ.ቅ.ተመ/

አሁን ደግሞ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ምሥጢረ ቁርባን ሥርዓት ከሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ጋር ያለውን ልዩነት በየፈርጁ እንመለከታለን:: በመጀመሪያም የምሥራቅ መለካውያን ግሪክ፣ ሩሲያ፣ ቡልጋሪያ፣ ሩማንያ፣ ቆጵሮስና ቤተሰቦቻቸውም ተለይተው የሚታወቁበት የቅዳሴ ሥርዓት አላቸው:: እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት ልዩ የመሥዋዕት መሥሪያ የላቸውም:: ለበረከት ከሚያመጡት ኅብስት ከተራ ዳቦ ቤት ገዝተው ነው:: ልዩ ምልክት ትንሽ ማኅተም በመካከሉ ላይ አለው:: ያውም በሙሉ ኅብስት ሳይሆን አስቀድመው ቆራርሰው ሸራርፈው ነው፣ የቅዳሴው ጸሎት የትምህርቱ ክፍል ካለቀ በኋላ መሥዋዕቱን በመንበር ላይ ያስቀምጡታል:: ፍሬ ቅዳሴውን የሚጀምሩት ከዚያ በኋላ ነው:: በቅዳሴም ጊዜ የሚነበቡ መጻሕፍት፣ ከጳውሎስ መልእክትና ወንጌል ነው:: ጳውሎስን የሚያነበው ዘማሪው /መሪጌታው/ ነው:: ከሊለም አስቀዳሾቹ ተራ ምእመናን ያነቡታል:: ወንጌሉን ቄሱ ያነባል፣ ዲያቆን ካለም ዲያቆን ያነበዋል:: ሥጋውና ደሙ ይለወጣል የሚሉት በ«ይረስዮ» ጊዜ ነው፣ ተለወጠ ካሉ በኋላ ለብ ያለ ውኃ፣

አምጥተው በጽዋው ይበርዙበታል። የሚያቀርቡትም ሥጋውንም ደሙንም አንድ ላይ ከጽዋው ነው። ጄኔቫ ሳለሁ አንድ የሕንድ ተዋሕዶ ቄስ ቀድሶ ሥጋውንም ደሙንም ከጽዋው ሲያቀርብ አይቼአለሁ። በእነዚህ ሀገሮች የሚያቀርበው ዲያቆን ካለ ዲያቆን፣ ከሌለም ቄስ ነው። በመጨረሻም ከቡራኬው ጋር ምእመናን እየገዙ ያመጡትን ኅብስት ቈራርሰው ለአስቀዳሾቹ ምእመናን ያድሏቸዋል። ይህም ኅየንተ ቁርባን ማለት ነው ይሉታል። ይህ በግብጽም አለ።

ከዚህ በኋላ ሡርሖተ ሕዝብ ይሆናል። የልዑካን ልክ የላቸውም፣ ሃያ ሠላሳ ሁነውም ይቀድሳሉ። አንድ ቄስ ብቻውንም ይቀድሳል። የቅዳሴ ሰዓት ሁልጊዜ ማለዳ ነው። በዐቢይ ጾም ከእሑድ ቅዳሜ በቀር ቅዳሴ ክልክል ነው። እሑድ የቀደሱበትን በጽዋው አስንብተው ዓርብና ረቡዕ በሌሎችም አመች በሆኑ ዕለታት ጸሎተ ሠርክ አድርሰው ያቀርቡታል። «ፕሮኢጊያዝሚኑ» አስቀድሞ የተቀደሰ ማለት ነው ይላሉ። ይኸም ብቻ ሳይሆን በጸሎተ ሐሙስ የቀደሱበትን እስከ ዓመት በመንበር ያስቀምጡታል፣ አቁርቡኝ የሚል በድንገት ቢመጣ «ለመጠባበቂያ ነው» ይላሉ። ከእኛ ጋር የሚመሳሰሉባቸው ሁለት ነገሮች ብቻ አሉ፣

ሀ. በአንድ መንበር ሁለት ጊዜ አይቀድሱም፣
ለ. ሁልጊዜ የሚቀድሱት በአኰቴት ነው።

ካቶሊካውያን ሥጋውና ደሙ ይለወጣል የሚሉት «ንሥኡ ብልዑ» በሚባልበት ጊዜ ነው። ከሥጋውም ከደሙም የሚቀበል ቀዳሽ ብቻ ነው። ለምእመናኑ ግን ሥጋውን ብቻ ያቀርቧቸዋል። ይህም «ሥጋዬን የበላ ደሜን የጠጣ የዘለዓለም ሕይወት አለው» ከሚለው አምላካዊ ቃል ጋር የማይስማማ ነው። ካቶሊኮች በምሥጢረ ቁርባን ከእኛ የሚለዩት በዚህ ብቻ አይደለም። ሌላም ብዙ አለ፦

ሀ. ከቁርስ በኋላ አንድ ሰዓት ቆይተው ይቆርባሉ ያቆርባሉ፣
ለ. በአንድ መንበር በአንድ ቀን መላልሰው ይቀድሳሉ፣
ሐ. መስገጃ ብለው በመንበሩ ላይ መሥዋዕቱን ያስቀምጣሉ፣
መ. የቅዳሴ ሰዓት ሁልጊዜም ማለዳ ነው።
ሠ. አንድ ቄስ ብቻውን ይቀድሳል። ከእኛ የሚለዩበት በእነዚህ በእነዚህ ምክንያቶች ሲሆን ከዚህም ሌላ ቀኖናቸው በየጊዜው ስለሚለዋወጥ ብዙ ለውጥ በቤተክርስቲያናቸው ይታያል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ የመንበሩን ገጽ ወደ ምዕራብ አዙረው ይቀድሳሉ ይባላል።

ከፕሮቴስታንቶች በቀር የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናትም ሆነ የሮማ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ሥርዓት ቢለያዩም ምሥጢረ ቁርባንን እንዴት እንደሚፈጽሙ አይተናል። በፕሮቴስታንቶች ዘንድ ምሥጢረ ቁርባን ለየት ያለ መልክ አለው። በእርግጥ ክህነትም ሥርዓትም ስለሌላቸው የሚሉትን ለማወቅ ያህል በመጠኑ እንመልከት። መሥዋዕት ብለው የሚያቀርቡት የተለየ ዝግጅት የላቸውም። ተራ ኅብስት ያቀርባሉ። በኅብስቱ አምሳል፣ ከኅብስቱ ጋር የክርስቶስ ሥጋ ይሰጣል ይላሉ። ይህም ማለት ኅብስቱ ምሳሌ መሣሪያ /Symbol/ ነው ማለት ነው። (In penotio in

pamo= «በኅብስቱ ውስጥ ከኅብስት ጋር»):: suli pame= «በኅብስቱ አምሳል»:: በአንቀጸ ተዋሕዶ መለካውያን የሚሉትን መሠረት በማድረግ የክርስቶስ አካል በኅብስቱ ያድርበታል ይላሉ:: ይህ ትምህርታቸው «ዝ፣ ውእቱ ሥጋዬ፣ ዝ ውእቱ ደምዬ »ያለውን ያፈርሰዋል:: እንደነሱ አባባል ኅብስቱ ምሣሌ ከሆነማ «ይህን ኅብስት ሳይገባቸው የሚበሉት ዕጻ ይሆንባቸዋል» ያለውን /ቀዳ.ቆሮ.11÷27/ የቅዱስ ጳውሎስ ትምህርት ምን ብለው ይተረጉሙታል:: ይህ የእነሱ አባባል ከቅዱሳን መጻሕፍትና ከቤተክርስቲያን ሊቃውንት ትምህርት የተለየ ነው:: የቤተክርስቲያን አባቶች ምሥጢረ ቁርባንን የማይመረመር ምሥጢር መሆኑን ያውቃሉ:: አርአያውና መልኩ ሳይለወጥ ልምላሜውና ጣዕሙ ሳይለየው ሥጋ መለኮት ደመ መለኮት ይሆናልና:: በእርግጥ ሥጋውና ደሙ ሲለወጥ አይታይም ቅዱሳን ግን ያዩታል:: በምዕራብ ቤተክርስቲያን ያሉ ሊቃውንት የኅብስቱም የወይኑም ባሕርዩ ይለወጣል ብለው ይናገራሉ /Transubstantial/:: የምሥራቅ ቤተክርስቲያ ሊቃውንት ግን በማይመረመር ግብር መለወጡን እንጂ የስንዴውም ሆነ የወይኑ ጥንተ ባሕርይ ለሁሉም ተለውጦ ይታያል ብለው አያምኑም::

## 4. ምሥጢረ ክህነት

ክህነት በግእዝ ቋንቋ «ተክህነ» «አገለገለ» ከሚለው ግሥ የወጣ ነው:: አገልግሎቱም ለሃይማኖት ብቻ ነው:: «ክህነት» የሥልጣኑ ስም ነው፣ አገልጋዮቹ «ካህናት» ይባላሉ:: ዕብራውያን ካህን ይሉታል:: አወጣጡ እንደ ግእዝ ነው:: የናናውያንም ኢየራቲቪን «ተክህኖ ተክህኖት» ከሚለው አርእስት «ኢየሬብአ» ብለው ያወጣሉ:: ካህን ማለት ነው:: ምሥጢረ ክህነትን የመሠረተው ራሱ ጌታ ነው፣ በደሙ የመሠረታትን ቤተክርስቲያንን የሚያገለግሉ ካህናት የአገልግሎት ሥልጣን የሚቀበሉት ከመንፈስ ቅዱስ ነው:: ይህ የካህናት ሹመት «ምሥጢረ ክህነት» ይባላል:: ምሥጢረ ክህነትን የመሠረተው ራሱ ጌታ ነው፣ በደሙ ቤተክርስቲያንን ከመሠረተ በኋላ ከትንሣኤው አያይዞ ለሐዋርያት ሥልጣነ ክህነትን ሰጥቷቸዋል:: /ዮሐ.20÷22-23/ ሐዋርያትም የትንሣኤውን አዋጅ ለመንገር ወደ ዓለም በገቡ ጊዜ በክህነታቸው ተአምራት ያደርጉ ነበር:: /ማር.16÷16/ ሐዋርያት በሥልጣናቸው ያሥሩ ይፈቱ ነበር:: /ማቴ.18÷18፣ ቀዳ.ቆሮ.4÷1፣ ካልዕ.ቆሮ.5÷20፣ ማቴ.16÷18/ ለምሳሌ የሐናንያንና የሚስቱን የሰጰራን የሲሞን መሠርይን ታሪክ ይመለከቷል:: /የሐዋ.5÷1-11፣ 8÷28-24/ ቤተክርስቲያንን ይመግቡና ያስተዳድሩም ዘንድ ሥልጣን ነበራቸው:: /የሐ.20÷15/ ይህም የማሰር የመፍታት ማለት «አውግዞ» ከቤተክርስቲያን አንድነት የመለየት፣ በይቅርታ ወደ ቤተክርስቲያን የመመለስ፣ ሥልጣን ምሥጢራትን የመፈጸም፣ ቤተክርስቲያንን የመመገብ ተልዕኮ እስከ ኅልፈተ ዓለም የሚቆይ መሆኑን ጌታ ተናግሯል:: /ማቴ.28÷20፣ ቀዳ.ቆሮ.11÷26/ ስለዚህ ሐዋርያትም ከጌታ ያገኙትን ሥልጣን ለተከታዮቻቸው አስተላለፉ:: እነሱ እስከ ዓለም ፍጻሜ አይኖሩምና:: ወዲያው ከኢየሩሳሌም ሳይወጡ በማስተንተን ተልዕኮ የሚረዷቸውን ሰባት

ዲያቆናት በምእመናን አስመርጠው በአንብሮተ እድ ሾመዋል:: /የሐዋ.ሥ 6÷6/ በርናባስና ጳውሎስም ቀሳውስትን ሾሙ /የሐዋ.ሥ 14÷23/ ቅዱስ ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ኤጲስ ቆጶስነት ሾመው:: /ቀዳ.ጢሞ.4÷14፣ ካልዕ ጢ. ሞ.1÷16::

በአዲስ ኪዳን በብዙ ቦታ ምእመናንን በጠቅላላ ካህናት ስለሚላቸው በፕሮቴስታንቱ /በረ. ማርያም/ ዓለም ያሉ አንዳንድ ቅርንጫፎች፣ «ክህነት የተለየ ሥልጣን ሳይሆን በክርስቶስ ላመኑ ሁሉ የተሰጠ የክብርና የማዕረግ፣ የባለሟልነት መጠሪያ /ደረጃ/ ነው» ይላሉ::

ለሐሳባቸውም ድጋፍ የሚጠቅሱት /ቀዳ.ጴጥ.2÷5–9፣ ራእይ 1÷7/ ነው:: በእርግጥ እሥራኤል ከግብጽ ከወጡ በኋላ እግዚአብሔር /የሆዋ/ በሙሴ አማካይነት የሰጣቸውን ቃል ኪዳን ይመስላል:: /ዘጸ.19÷5–6:: ይህ ቃል አሻሚና አደናጋሪ አይደለም:: ጴጥሮስም ዮሐንስም የተናገሩት የብሉይ ኪዳኑን የ ቃል ኪዳን አነጋገር በመንፈሳዊ ምሥጢር ተርጉመው ነው:: «ካህን» የሚለው ቃል መሠረቱ ብሉይ ኪዳን እንደመሆኑ መጠን የሚያሳየው ባለሟልነትን ቀራቢነትን ተወዳጅነትን ነው:: ቃሌን ብትጠብቁ ካህናት ትሆናላችሁ ብሎ እግዚአብሔር ለእሥራኤል የተናገረውን ቃል የሚገልጥ ነው::

የአሮንን ክህነት መደምሰሱ አልነበረም:: ሕዝቡን በእምነት ለባለሟልነት መምረጡ ነበር እንጂ:: በሐዲስ ኪዳንም የጴጥሮስና የዮሐንስ ንባብ ቀራቢነትን ባለሟልነትን ተወዳጅነትን በክርስቶስ የተገኘውን የጸጋ መጠን መናገራቸው ነው እንጂ ጌታ ለሐዋርያት የሰጠውን የአገልግሎት ሥልጣን መሻራቸው አይደለም:: በክርስቶስ ያመኑ ምእመናን ካህናት ብቻ ሳይሆኑ ነገሥታትም ይባላሉ፣ /ራእየ ዮሐ.5÷10/ ይህም የሚያሳየው በጥምቀት በልጅነት የተገኘውን የጸጋ ልዕልና ነው:: የማዕረጋት ቁንጮዎች እነዚህ ሁለቱ ናቸውና ክህነትና መንግሥት:: መጽሐፍ ቅዱስ ምእመናንን «ካህናት ነገሥታት» የሚላቸው ጸጋ መንፈስ ቅዱስን መቀባታቸውን ለመግለጥ ነው:: ሐዋርያት በአንብሮተ እድ የተሾሙትን አሁንም በሐዋርያዊት ቤተክርስቲያን የሚያገለግሉ ካህናት በየጊዜው በኤጲስ ቆጶሳት አንብሮተ እድ የሚሾሙትን ሹመት የሚሽር አይደለም:: ይህን አንጋዶ ተርጉሞ «ካህን ነኝ ካህን አያስፈልገኝም ንጉሥ ነኝ መሪ አያስፈልገኝም» የሚል ክርስቲያን ነኝ ባይ በገዛ አጁ ዕዳ ይገባል:: የቤተክርስቲያንም ቋንቋ እንዳልገባው ያሳያል::

ክህነት በቤተክርስቲያን ሦስት ደረጃ አለው:: ዲያቆን፣ ቄስ፣ ኤጲስ ቆጶስ፣ እነዚህ ሦስቱም በሥራና በማዕረግ የተለያዩ ይሁኑ እንጂ ሁሉም የየራሳቸው ተልዕኮ አላቸው:: በሐዲስ ኪዳን በአንዳንድ ቦታ በቄሱ ስም ኤጲስ ቆጶሱ፣ በኤጲስ ቆጶሱ ስም ቄሱ ይጠራበታል:: ይህም የስም እንጂ የሥልጣን ሞክሼ አይደለም:: ሐዋርያት ጳጳሳት ኤጲስ ቆጶሳት ናቸው:: ቀሳውስትን ዲያቆናትን ይሾማሉና:: በአንዳንድ ቦታ ደግሞ ቀሳውስት እያለ ይጠራቸዋል፣ «እመኒ ቀሲስ» /ዮሐ.ካል.1÷1::/ ዲያቆናትም ይላቸዋል:: /ቀዳ.ቆሮ.3÷5::/ ካልዕ ቆሮ.3÷6:: ሐዋርያት ኤጲስ ቆጶሳት ቀሳውስት፣ ዲያቆናት ቢባሉም በሦስቱም ሥልጣናት ሠርተውባቸዋል፣

ሦስቱም ሥልጣናት ተሰጥተዋቸዋልና። ጳጳሱ ቅስና፣ ዲቁና የለህም አይባልም። አቡን ቄስ ናቸው ቢሉ ተርጓቸው ለሌላ ይናኙሉ እንደተባለው። ነገር ግን ይህን አጠራር ምክንያት አድርገው አንዳንድ የፕሮቴስታንት ቅርንጫፎች ሦስቱን የክህነት ደረጃዎች አይቀበሉም፣ በእነሱ ትምህርተ ክህነት የሚባለው ቅስና ብቻ ነው። እሱም እንደ ሐዋርያት ቤተክርስቲያን ሥርዓት በአንብሮተ እድ በቅባት ሳይሆን እገሌን መርጠናል ብለው አማኞቻቸው በሚሰጡት ድምጽ ነው። በእነሱ አባባል የኤጲስ ቆጶሳት ማዕረግ የክህነት ደረጃ አይደለም።

በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የምንገለገልባቸው ሦስቱ የክህነት ደረጃዎች በሐዲስ ኪዳን ግልጥ መረጃ አላቸው። ሐዋርያት ራሳቸው ኤጲስ ቆጶሳት ነበሩ፡፡ ይኸውም ቀሳውስትን ዲያቆናትን በመሾማቸው ይታወቃል። ጢሞቴዎስና ቲቶ ቀሳውስትን የመምራትና የማስተዳደር ሥልጣን ነበራቸው። የኤጲስ ቆጶስነት ሥልጣን ነበራቸው። /ቀዳ.ጢሞ 5÷19 ቲቶ.1÷5/ ቀሳውስት ሹመት /የሐዋ.ሥራ 14÷23/ ዲያቆናትም ከቀሳውስት በታች ደረጃ አላቸው። አገልግሎታቸውም የተለየ ነው። /የሐ.ሥ6÷2/ በቤተክርስቲያን አባቶችም ዘንድ ሦስቱ የክህነት ደረጃዎች የታወቁ የተጠበቁ ናቸው። ለምሳሌ የአንጾኪያው ሊቀ ጳጳስ አግናጥዮስ /107/ ስለ ሦስት ማዕረጋት መኖር ግልጥና ጭብጥ ያለውን መረጃ ይሰጠናል። ለኤፌሶን ምእመናን በላከው የምክርና የተግሳጽ መልእክት እንዲህ ይል ነበር «ለእግዚአብሔር የሚገባችሁን ሁሉ ለማድረግ ፍጠኑ የሚመራችሁ ኤጲስ ቆጶስ የእግዚአብሔር እንደራሴ ነው። ቄሱም እንደ ሐዋርያት፣ ዲያቆናትም ለክርስቶስ ቤተክርስቲያን ባለአደራዎች ናቸውና»። እነዚህ ሦስቱ የክህነት ደረጃዎች ከፕሮቴስታንት ዓለም በቀር በሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ይሠራባቸዋል።

## የክህነት አሰጣጥ

በቤተክርስቲያን ትውፊት መሠረት ክህነት የሚሰጠው ከጸሎትና ከምሕላ ጋር በምርጫ በዕጣ ነው። ይህንንም በይሁዳ መንበር በተተካው በማትያስ ምርጫና ዕጣ ማየት ይቻላል። /የሐ.ሥ1÷24/ የሰባቱም ዲያቆናት ሹመት በምርጫ ነው። የሐ.ሥ.6÷6። ከሁሉም በፊት ደግሞ ሐዋርያት በራሱ በጌታ ተመርጠው ተሾመዋል። ማቴ.10÷1። 28÷19/ ዮሐ.15÷16።/ የጳውሎስም ጥሪ ምርጫ ነው/ የሐዋ.ሥ.9÷1–18/ ገላት.1÷1።/ ጳውሎስና በርናባስ እንደገና ተመርጠዋል። የሐዋ.ሥ13÷2–3። 20÷28 በቤተክርስቲያን ታሪክ፣ ይልቁንም በመሥጢረ ቤተክርስቲያን እንደሚታወቀው ለክህነት የታጩት ሰዎች ተመርጠው ሲቀርቡ የመሾም ሥልጣን ያላቸው ደግሞ ጸሎትና ምሕላ አድርሰው በአንብሮተ እድ ይሾማሉ። በአንብሮተ እድ መሾም፣ በአንብሮተ እድ መባረክ በአንብሮተ እድ ሥልጣን ማስተላለፍ፣ መብት መስጠት ከብሉይ ኪዳን ቀደም ሲልም የተለመደ ነበር። ለምሳሌ ያዕቆብ የልጅ ልጆቹን ምናሴንና ኤፍሬምን በአንብሮተ እድ ባርኮ ከልጆቹ እኩል እንዲወርሱ ሥልጣንና መብት ሰጥቷቸዋል። ዘፍጥ.48÷14–17። በብሉይ ኪዳንም ሌዋውያን የሚሾሙት በአንብሮተ እድ

ነበር:: /ዘኁ.27÷23/ ሙሴ በአንብሮተ እድ እሥራኤልን የሚመራበትን ሥልጣን ለኢያሱ አስተላልፎለታል:: /ዘዳ.34÷9/ ለእግዚአብሔር የሚቀርበውን መሥዋዕት በአንብሮተ እድ ይባርኩት ነበር:: /ዘሌ.1÷14/

በአዲስ ኪዳን የአንብሮተ እድ ሹመት ጌታ በአንብሮተ እድና በንፍሐት /በቅብዐት/ ሐዋርያትን ሹሚቸዋል:: /ዮሐ.20÷23–24፣ ማር.10÷16፣ ሉቃ24÷50–51/ ሐዋርያትም ከላይ እንደገለጥነው በአንብሮተ እድ ይሾሙ ነበር:: ኤጲስ ቆጶሳትም ይህንን ሥርዓት በአንብሮተ እድ ይሾማሉ::

ከሦስቱ የክህነት ደረጃዎች ሌላ:– ማለት ከድቁና፣ ከቅስና፣ ከኤጲስ ቆጶስነት ሌላ በቤተክርስቲያን የታወቁ የውስጥ ክፍልፋይ ማዕረጋት አሉ:: እነሱም አንባቢ፣ ንፍቅ ዲያቆን፣ መዘምር፣ በረኛ ናቸው:: በፍትሕ መንፈሳዊ እንደተገለጠው «ዲያቆናውያት» የሚባሉ ሴቶች የቤተክርስቲያን አገልጋዮች ነበሩ: እነዚህ ሴቶች ቤተክርስቲያኝን ለብዙ ዘመናት ሲያገለግሉ የኖሩ ናቸው:: ይልቁንም በዘመነ ሰማዕታት ለሰማዕታት በመላላክ ሰማዕታት ሲታሠሩ ስንቅ በማቀበል፣ አዲስ አማንያን ሲመጡም ሴቶቻቸውን በማስተማር መመሪያም በመስጠት ብዙ አገልግሎት ሲያበረክቱ ኑረዋል:: የእነዚህ ዲያቆናውያት «አሿሿም» እንዴት እንደሆነ በቅዱስ መጽሐፍም ሆነ በቤተክርስቲያን አባቶች ድርሳን ፍንጭ የለም:: ለጢሞቴዎስ በላከው ምክርና መመሪያ ቅዱስ ጳውሎስ «ከሠላሳ ዓመት ያላነሣት» የቤት እናት ምረጥ ብሎታል /ቀዳ.ጢ ሞ.5÷9/ ከዚህ ሌላ ስለ ዲያቆናውያት ሹመት በቅዱስ መጽሐፍ የሚታወቅ የለም:: ኤጲስ ቆጶሱ በማይገኝበት ቦታ እንደ ኤጲስ ቆጶስ ሆኖ የሚያገለግል /ዛሬ ኤጲስ ቆጶስ ቆሞስ በቤተክርስቲያናችን ይሾማል:: የቁምስና ሹመት የሚሰጠው በኤጲስ ቆጶስ ነው:: ቆሞስ የሚሆኑት በድንግልና የመነኮሱ የቅስና ማዕረግ ያላቸው ናቸው:: ቆሞሳት አዲስ ቤተክርስቲያን ይባርካሉ፣ አዲስ ጽላት ግን አይባርኩም:: ክህነት አይሰጡም:: ሜሮን አያፈሉም:: የቁምስና ማዕረግ የሚገባቸው የገዳም አበምኔቶች ናቸው::

ወደ ክህነት መምጣት የሚገባቸው እነማን መሆን አለባቸው? ክህነት ከመቀበሉ በፊት እጩው ካህን ሃይማኖቱን ጠንቅቆ እንዲያውቅ ያስፈልጋል /ጉባኤ ኒቅያ 325 ቀኖና.19/ ከአዲስ አማንያን መሆን የለበትም/ ቀዳ.ጢ.ሞ3÷6:: ቀኖና ሐዋ.80 ጉባኤ ኒቅያ 325 ቀኖና 2–9:: የሊዶቅያ ቀኖና 12/ ቅዱሳት መጻሕፍትንና ቀኖና ቤተክርስቲያንን የሚያውቁ ከዚህም ጋር ሙሉ አካልና የመንፈስ ጤንነት ያላቸው ካህናት እንዲሾሙ ታዟል:: /የሐዋ.ቀኖና 78/ ኤጲስ ቆጶስ ወይም ቄስ በሚካንበት ጊዜ ዕድሜው ከ30 ማነስ የለበትም:: ዲያቆንም ሲሾም የ25 ዓመት እንዲሆን ታዟል:: ዲያቆናት ሚስት ካገቡ በኋላ ወይም መንኩሰው የቅስና ማዕረግ ይቀበላሉ:: ቀዳ.ጢ.ሞ.3÷2 4÷12:: የሐዋርያት ቀኖና 4/የስድስተኛው ሲኖዶስ ቀኖና 13/ የጋንግራ ሲኖዶስ ቀኖና 4:: /ኤጲስ ቆጶሳት ለመሆን መብት ያላቸው ግን በድንግልና የመነኮሱ የቅስናና የቁምስና ማዕረግ ያላቸው ናቸው:: /የስድስተኛው ጉባኤ ቀኖና 12/ ማዕረገ ዲቁና ከተቀበሉ በኋላ ሚስት ለማግባት ይቻላል:: /የዕንቆራ ጉባኤ ቀኖና 10::/ የቅስና ማዕረግ ከተቀበሉ

በኋላ ግን ለማግባት አይቻልም:: /የሐዋ.ቀኖና 26:: የቅድሎስ የትሩሎስ ሲኖዶስ ቀኖና 6 የኒቅያ ቂሣርያ ቀኖና 1:: ቀኖና ኒቅያ 325÷3–6:: የባስልዮስ ቀኖና 6::/ እነዚህን ቀኖናዎች በማያፋልስ ሥርዓት ኤጲስ ቆጶስ በፓትርያርኩ መሪነት በሲኖዶስ አባላት ይሾማል:: ቤተክርስቲያን በችግር ላይ በምትገኝበት ጊዜ ግን በሁለት ኤጲስ ቆጶሳት ይሾማል:: /የሐዋ.ቀኖና 8÷4/ የሚሾመውም በአንብሮተ እድ፣ በቅብዐት፣ ነው:: ኤጲስ ቆጶሱ፣ ቄሱም ሆነ ዲያቆኑ ሲሾሙ ጸሎተ ሃይማኖትን አስምተው አንብበው ቤተ ክርስቲያን የምትቀበላቸውን ጉባኤዎችና ውሳኔዎቻቸውን ቆጥረው እናከብራለን እናስከብራለን፣ ብለው ቤተክርስቲያን የማትቀበላቸውን ግን አውግዘው ይሾማሉ::

የቤተክርስቲያን ክህነት ከምኩራቡ ዘርዐ ክህነት የተለየ ነው :: የምኩራቡ ክህነት ሌዊንና አሮንን መሠረት አድርጐ ነው:: በእነሱ የዘር ሐረግ ብቻ የሚተላለፍ ነው:: የቤተክርስቲያን ክህነት ግን ክርስቶስን መሠረት አድርጐ ነው፣ የዘርና የጐሳ ልዩነት አይደረግበትም:: የብሉይ ኪዳን ካህን የሚሾመው መሥዋዕተ ኦሪትን ለመሠዋት ነው:: ማለት ስብ ለማጤስ ደም ለማፍሰስ ነው:: የሐዲስ ኪዳን ክህነት መሠረት ክርስቶስ ግን የራሱን ደም አፍሶ የፈጠረውን ያዳነ እንደመሆኑ መጠን በእሱ የተሾሙ ሐዋርያትና ወራሾቻቸው ኤጲስ ቆጶሳትና ካህናትም የሚሾሙት ዓለምን በእርሱ ለማሳመን ነው፣ መሥዋዕቱም ቁርባኑም የክርስቶስ ሥጋና ደም ነው:: በቤተክርስቲያን ሕግና ሥርዓት መሠረት ሦስቱም የክህነት ደረጃዎች ለእያንዳንዳቸው የተወሰነ ተልእኮ አላቸው::

## ሀ. የኤጲስ ቆጶስ ተልዕኮ:–

ቀሳውስትን፣ ዲያቆናትን፣ ይሾማል፣ ያስተምራል ያጠምቃል ያቆርባል:: ከዚህም ሁሉ ጋር በሀገረ ስብከቱ ያሉት ምእመናን በመንፈሳዊና በማኅበራዊ ኑሮ ችግር ሲደርስባቸው ችግራቸውን ያቃልላቸዋል:: እንደ አባት፣ እንደ አለቃ ሆኖ ይመክራቸዋል:: እንደ ዳኛም ሁኖ ይፈርድላቸዋል:: እነሱም እንደ ልጅ ይታዘዙለታል፣ ከፈቃዱ አይወጡም:: አግናጥዮስ እንዳለው፣ «በክርስቶስ አምሳል በክርስቶስ የማስተማሪያ ቦታ /ዙፋን/ የተቀመጠው ኤጲስ ቆጶስ ምእመናንን የሚማርክ ቃና ያለው ትምህርት ለመስጠት የሚችለው ምእመናንና ካህናት የእርሱን አባትነት ሲያውቁለት እሱም እንደአባት ሲያስብላቸው ነው:: መሰንቆ እንኳ ይላል አግናጥዮስ አድማጮችን የሚማርከው ጭራዎቹ ከእንጨቱ ጋር ተስማምተው ሲወጠሩና ሲቃኙ ነውና:: ዮሐንስ አፈወርቅም:– የኤጲስ ቆጶሱ ሥራ ምእመናንን ለጸሎት ማትጋት መሆኑን ሲገልጥ «ኤጲስ ቆጶስ ሆይ ሕዝቡን ጧትና ማታ ለነግህና ለሠርክ ጸሎት በቤተክርስቲያን ይገኙ ዘንድ እዘዛቸው» ብሏል::

## ለ. ቀሳውስት

እንደ ኤጲስ ቆጶሱ ማስተማርና ማጥመቅ እንዲሁም ማቁረብ ነው:: በተረፈም ኤጲስ ቆጶሱ ባልተገኘበት ቦታ በኤጲስ ቆጶሱ የተወከለውን የእርሱን ሥራ ይሠራሉ:: ቀሳውስትን ዲያቆናትን መሾም ሜሮን ማፍላት፣ አዲስ ቤተክርስቲያን መባረክ አይችሉም:: ቀሳውስት በሕግ በተክሊል ያገቡ ናቸው፣ በድንግልና የመነኩሱም ቅስና ማዕረግ ከተቀበሉ ቀሳውስት ይባላሉ:: ቀሳውስት ናቸው:: ለነዚህም በሌሎች አገሮች ልዩ መጠሪያ አላቸው /ኢየሮመናሆስ/ ይባላሉ:: በእኛ ግን መነኩሴ ይባላል እንጂ ልዩ መጠሪያ የለውም:: መነኩሴ መባል ደግሞ ሥልጣነ ክህነት ላለውም ለሌለውም መጠሪያ ስለሆነ ያሾግል::

## ሐ. ዲያቆናት

ዲያቆናት የኤጲስ ቆጶሱና የቄሱ ተላላኪዎች ናቸው:: ምሥጢራትን የመፈጸም መብት የላቸውም:: «እስመ እሙንቱ ከመ ሕዝብ» ቁጥራቸው ከምእመናን ነው:: ንፍቅ ዲያቆን የሚባለው ዋናውን ዲያቆን ይረዳል:: አንባቢ /አናጉንስጢስ/ የሚባለው በቤተክርስቲያን በተለይም በቅዳሴ ጊዜ የሚነበቡትን ምንባባት ያነባል:: መዘምር /ደብተራ/ ደግሞ ስሙ እንደሚያስረዳው በቤተክርስቲያን መዝሙር የሚዘምር የሚያቀነቅን ማለት ነው:: ሌሎቹ እሱን እየተከተሉ ይዘምራሉ:: ኃፃዌ ኆኅት /በረኛ/ ደግሞ ቤተክርስቲያንን ይጠርጋል፣ ያጠዳል፣ ያነጥፋል፣ ይደውላል: ቤተክርስቲያንን በጸሎት ጊዜ የሚከፍት ጸሎቱ ሲፈጸም የሚዘጋ ነው::

ኤጲስ ቆጶሳት ሥልጣናቸው አንድ ሲሆን ሊቀ ኖሎት ሆነው በሚሾሙበት ቦታ ባለው ስፋትና ታሪክ መሠረት የተለያዩ የማዕረግ ስም አላቸው:: በአውራጃና በወረዳ የሚሾሙት ኤጲስ ቆጶሳት ይባላሉ:: አውራጃው ወረዳው፣ ሰፋ ያለ ሲሆን ለማስተማርና ለማጥመቅ እንዲያመች ኤጲስ ቆጶሱን ለመርዳት የሚሾሙ ኮሬ ኤጲስ ቆጶስ /ሆር ኤፒስኮፒ/ የሚባሉ አሉ:: የገጠር ኤጲስ ቆጶሳት ማለት ነው፣ ሥልጣናቸው እንደ ኤጲስ ቆጶሱ ሆኖ በአስተዳደር ግን በእርሱ ሥር ናቸው:: በአጠቃላይ ግዛቱ ከተማ ማለት እንደ መቀሌ፣ እንደ ደብረ ማርቆስ እንደ አርባ ምንጭ፣ ባሉት ከተሞች የሚሾሙት ደግሞ መጥሮጶሊስ /ሜትሮፖሊቲስ/ ይባላሉ:: «የእናት ከተማይቱ ኤጲስ ቆጶስ ማለት ነው» እንደ አውራ እንደ አለቃ ሆኖ በሀገረ ስብከቱ ውስጥ በአውራጃውና በየወረዳው ያሉትን ኤጲስ ቆጶሳት ኮሬ ኤጲስ ቆጶሳት ይመራል ያስተዳድራል:: ይህ ማዕረግ በመጀመሪያ የተወሰነው በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በጉባኤ ኒቅያ ነው:: /ጉባኤ ኒቅያ 325 ቀኖና 4::/ ሁለተኛው ማዕረግ ሊቀ ኤጲስ ቆጶስ ወይም ርእሰ ኤጲስ ቆጶስ የሚባለው ነው:: በዚህ ማዕረግ ስም እንደ ላሊበላ እንደ ደብረ ሊባኖስ ባሉ ቦታዎች የሚሾመው ኤጲስ ቆጶስ የሚጠራበት ነው:: አትናቴዎስ ሁልጊዜ የእስክንድርያውን ኤጲስ ቆጶስ እለእስክንድሮስን ሊቀ ኤጲስ ቆጶስ እያለ ይጠራው ነበር:: እስክንድርያ በጥንታዊ ታሪኳ የታወቀች ነበረችና::

ፓትርያርክ የሚባል የማዕረግ ስም የተጀመረው በ5ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ነው። በዚህ የማዕረግ ስም የሚጠሩ፣ በመጀመሪያ የሮም፣ የእስክንድርያና የአንጾኪያ መጥሮፖሊሶች ነበሩ፡፡ ኋላ ግን ራሳቸውን ችለው የሚተዳደሩ አገሮች ሁሉ የየራሳቸውን ፓትርያርክ ሹመዋል። ፓትርያርክ ማለት በዕርሁ ሊቀ አበው ማለት ነው። በመጨረሻም «ፖፕ ፖፕ፣ ፓፓ»የሚባለው ማዕረግ ከአምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻ ጀምሮ ለሮምና ለእስክንድርያው ሊቃነ ጳጳስ ቀጳሳት የተሰጠ ስም ነው። /ጎርጎርዮስ ዘቂሳርያ ቀኖና1/፡፡

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሥርዓት ሦስቱ ዐበይት የክህነት ማዕረጋት ዲቁና፣ ቅስና፣ ኤጳስ ቆጳስ ናቸው። አራቱ ንዑሳን ማዕረጋት ደግሞ <u>ንፍቀ ዲቁና፣ አንባቢነት፣ መዘምርነትና ኃጻዌ ኆኅት</u> ናቸው። በአጠቃላይ ሰባቱም ማዕረጋት ይሠራባቸዋል። ከነዚህ ሌላ « ሥልጣነ ቡራኬ» የሚባል ላልተማሩ ሰዎች የሚሰጥ ፈቃድ አለ። በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ምእመናኑ ምግባቸውን ሲመገቡም ጸሎቱን የሚመራው የቤቱ ባለቤት ነው። በቤት ውስጥ ከብትም ቢታረድ አስቀድሞ በእግዚአብሔር ስም መባረክ ስላለበት ይህንኑ ለማድረግ ከጳጳሱ ዘንድ እየሄዱ ልዩ ፈቃድ /ቡራኬ/ ይቀበላሉ። ጳጳሱም የቡራኬ ጸሎት አድርሶ ባርኮ ያሰናብታቸዋል። ከዚያ በኋላ ከብትም ለማረድ ማዕዳቸውንም ባርከው ለመቁረስ ደስ ይላቸዋል። ከዚህ ቀጥለን ዐበይት የክህነት ማዕረጋት የዲቁና፣ የቅስና፣ የኤጳስ ቆጳስነት ማዕረጋት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን እንዴት እንደሚሠራባቸውና ከሌሎቹም ያለውን ልዩነት ባጭሩ እንገልጣለን።

ሀ. <u>ዲያቆንና ቄስ፡-</u> በቤተክርስቲያን የዲቁና ማዕረግ የሚሰጠው ከጋብቻ በፊት ነው። በኋላ በተክሊል አግብቶ የቅስና ማዕረግ ይቀበላል። ከቅስና ማዕረግ በላይ ያለውን ማዕረግ አያገኝም። ዲቁናውን እንደተቀበለ ለመመንኮስ ቢፈልግ ግን ገዳም ገብቶ ረድቶ/ በረድእነት አገልግሎ/ ይመነኩሳል። ከመነኮሰ በኋላ የቅስና ማዕረግ ይቀበላል። ለቁምስናና ለኤጳስ ቆጳስነትም መንገዱ ይህ ነው።

በምሥራቅ የመለካውያን ሥርዓት የድቁና ማዕረግ የሚቀበለው ካገባ ወይም ከመነኮሰ በኋላ ነው። የዲቁና ማዕረግ ከተቀበለ በኋላ ማግባት ክልክል ነው። ሳይመነኩስ በድንግልናው ብቻ ዲቁና ተቀብሎ ከዚያው ላይ ቅስና ይሰጡታል፣ ይህም ላለማግባት መወሰኑን ካረጋገጡ በኋላ ነው። ይህ ግን ቢቸግር ነው እንጂ እነሱም ጥሩ ነው ብለው አያምኑበትም። ክህነቱን የሚያጐድፍ ወንጀል ካልሠራ አይሻርም።

በላቲኖች /በካቶሊኮች/ ሥርዓተ ክህነት ወደ ክህነት ለሚቀርብ ሁሉ ማግባት ክልክል ነው። በፕሮቴስታንቶች /ፀረ ማርያሞች/ ግን ክህነትን ምሥጢር ብለው ስለማይቀበሉት እንኳን አንድ ጊዜ ሁለተኛ ያገባም ቄስ ይሆናል። ቄስ ከተባለ በኋላም ያገባል። አሿሿሙም ምሥጢራዊነት የለውም። እንደ ጭቃ ሹም እንደምስለኔ ለተወሰነ ጊዜ /ወራት/ ነው። የአገልግሎቱ ወራት ሲፈጸም ይሻራል።

ሰ. ኤጲስ ቆጶስ፡- በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሥርዓት ኤጲስ ቆጳስነት የሚሾመው ከቆሞሳት መካከል በትምህርቱ በትሩፋቱ ልቆ የተገኘ አባት ነው:: የሚመረጠውም በሲኖዶስ ነው::

በምሥራቅ መለካውያንም ኤጲስ ቆጳስነት የሚሾሙት ደናግል መነኮሳት ናቸው የሚመረጡትም በሲኖዶስ ነው::

በሮማ ካቶሊክ ሥርዓት ካህናቱ በሙሉ ያላገቡ ይሁኑ እንጂ ዓለማውያንና ገዳማውያን ተብለው ከሁለት የተከፈሉ ናቸው:: አብዛኛውን ጊዜ ጳጳሳት፣ ካርዲናሎችና ፓፓዎችም የሚመረጡት ዓለማውያን ካህናት ከሚባሉት ነው::አልፎ አልፎ ግን ከገዳማውያኑም ይሾማሉ:: ፕሮቴስታን ቶች የተወሰነ ቀኖና የላቸውም:: ሁሉም ያገባ ነው::

## 3. ምሥጢረ ንስሐ

ክርስቲያን በጥምቀት ከዓለም ክፉ ሥራዎች ሁሉ የተለየ ነው:: የሞተ ነው:: ሰው ሠራሽ ሕግ ማለት:- ይህን አድርግ ይህን አታድርግ የሚሉትን ሕጎች ተላልፎ አይበድልም /ሮሜ.6÷3፣ ቆላ.3÷5-12፣ ገላ.2÷29፣ 5÷24/:: ሕይወቱ ለክርስቶስ የተሰጠ ነው /ሮሜ 12÷1-2/:: የመጨረሻ ግቡና ዓላማውም ክርስቶስ ነው:: /ፊል.2÷5፣ ቀዳ.ጴጥ2÷21-24::/ የመንፈሳዊ ኃይሎች ምንጭና መገኛ ክርስቶስ ነው:: /ዮሐ.6÷48፣ ካል.ቆሮ.12÷9፣ ኤፌ.4÷16/:: አካሉ የመንፈስ ቅዱስ መቅደስ ነው /ቀዳ.ቆሮ.6÷19/:: በአጠ ቃላይም የክርስቶስ ሕዋስ ነው፣ ስለዚህ በክርስቶስ አምኖ የተጠመቀ ክርስቲያን ሁሉ ንጽሕናና ቅድስና ገንዘቦቹ ናቸው:: የክርስቶስን አካል ለማቆሸሽ አይፈቀድለትም:: /ቀዳ.ቆሮ.6÷15/ ከዚህ በላይ እንደገለጥነው ቅዱሳት መጻሕፍት የክርስቲያንን ማንነትና ያለበትንም ደረጃ አጣርተው የገለጡት ክርስቲያን በዓለም ፈተና የለበትም ፈተና አይቀርበውም ለማለት አይደለም:: እንዲያውም ክርስቲያን በዚህ ጊዜያዊ ሕይወቱ የክርስቶስን መስቀል ተሸክሞ የሚጓዝ ነው:: ብዙ ጸዋትወ መከራ አለበት፣ ነገር ግን የዓለምን ክፋት ድል ያደረገ ክርስቶስን አምኖ በክርስቶስ መስቀል ፈተናዎቹን ሁሉ ድል ያደርጋል:: ክርስቲያኖችን በዓለም ብዙ መከራ እንደሚገጥማቸው ክርስቶስም አልሰወረውም:: «በዓለም ብዙ መከራ ያገኛችኋል ነገር ግን እኔ ዓለምን አሸንፌአለሁና እናንተም አሸንፉ» ብሎ ለክርስቲያኖች አስተምሯል:: /ዮሐ.16÷33/

በቤተክርስቲያን ብዙ ጊዜ ሲያወዛግብ የኖረው ሰው በጥምቀት ከውኃና ከመንፈስ እንደገና አዲስ ሰው ሆኖ ከተወለደ በኋ እንዴት ሊመለስ ይችላል? የሚለው ጥያቄ ነበር:: ይህንንም ይዘው አንዳንድ የቤተክርስቲያን አባቶች «ብርሌ ከነቃ አይሆንም ዕቃ» ከጥምቀት በኋ የበደለ ሰው ለመመለስ አይችልም እያሉ አስተምረዋል፤ ሌሎቹ ደግሞ ባይበዛም አንድ ጊዜ ቢሳሳት በንስሐ /በኑዛዜ/ ሊመለስ ይችላል እያሉ ያስተምሩ ነበር:: ይሁን እንጂ እስከ አምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ በይፋ ሲሠራበት የኖረው ትምህርት ከጥምቀት በኋ መሳሳት አይኖርም

የሚለው ነበር፣ ይህንንም በመፍራት በዚያ ዘመን የነበሩ ሰዎች ሁሉ የክርስትናን ትምህርት አምነው ቢቀበሉም የሚጠመቁት ካረጁና ካፈጁ በኋላ እንዲያውም በሞት አፋፍ ላይ ሲሆኑ ነበር:: ከአምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በኋላ ግን የምእመናን ቁጥር እየጨመረ ስለሄደ ለምእመናን መግቦት ሲሉ የቤተክርስቲያን አባቶች ሰብዓ ጊዜ ሰባት ቢበድልህ ይቅር በለው ብሎ ጌታ ለጴጥሮስ ያስተማረውን የንስሐ ትምህርት /ማቴ.18÷22/ መሠረት አድርገው በድንገተኛ ሁኔታ ከምእመናን ውስጥ የበደሉ ቢኖሩ በንስሐ ሊመለሱ ይችላሉ እያሉ ማስተማር ጀመሩ:: ንስሐ ከሰባቱ ምሥጢራት ቤተክርስቲያን አንዱ የሆነው ከዚያ ጀምሮ ነው:: በቤተክርስቲያን ትምህርት:- ሰው ከተሳሳተ ሁለት ነገሮች ያስፈልጉታል::

ሀ/ ንስሐ ለ/ ኑዛዜ

ሀ. <u>ንስሐ</u>:- ማለት «ነስሐ» ተጸጸተ፣ ተቆረቆረ፣ ከሚለው የግእዝ ግሥ የወጣ ነው:: ሊሠሩት በማይገባ ሥራ ወይም ኃጢአት ማዘን፣ ምነው ባልሠራሁት ምነው ባላደረግሁት፣ ምን ቀን ጣለኝ፣ ብሎ መቆጨት ነው:: የሚጸጸት ፍጡር ሰው ብቻ ነው:: ሌሎች ፍጥረታት የመጸጸት፣ ስሜት የላቸውም::

ለ. <u>ኑዛዜ</u>:- ማለት ደግሞ ሰው አንድ ሥራ ከሠራ በኋላ ያንኑ ሳይደብቅ ሳይቀንስ ጨርሶ መናገር ማለት ነው:: ንስሐ ለማንኛውም የጸጸት መግለጫ ይሆናል:: ኑዛዜም እንደዚሁ ነው:: ኃጢአትን መናገር ብቻ ሳይሆን ማንኛውም ሰው ሊሞት ሲል ሀብቴን ንብረቴን ለእገሌ ሰጥቻለሁ ብሎ በቄስ ፊት የሚናገረው የመጨረሻ ንግግር ኑዛዜ ይባላል:: በዚህ ላይ የምንገልጠው የንስሐና የኑዛዜ ፍች እንደሚከተለው ነው::

በሐዲስ ኪዳን «ንስሐ» ከማመን ጋር የተያያዘ ነው:: /ማቴ.4÷17/ ሐዋርያትም ያስተማሯቸውን አይሁድና አሕዛብ የሚያጠምቋቸው ከንስሐና ከኑዛዜ ጋር አያይዘው ነበር:: /የሐ.ሥ.2÷28/ ከክፉ ሥራ ወደ ደግ ምግባር መመለስ ካለማመን ወደ ማመን መምጣት ነውና:: ይህን ትምህርት መሠረት አድርጋ ቤተክርስቲያን እስከ ዓለም ፍፃሜ ስትሠራበት ትኖራለች:: ንስሐና ኑዛዜ ሁለት የተለያዩ ቃላት ቢሆኑም ተደጋጋፊነት አላቸው፣ ከሁለቱ አንዱ ከጠፋ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ አይገኝምና፣ ለምሳሌ ተነሳሒው በፈጸመው ስሕተት ከልብ ተጸጽቻለሁ ብሎ ከኑዛዜው ከፍሎ ቢያስቀር የሃይማኖት ጉድለት ነው ወይም ልቡናው በሐዘን ሳይሰበር የዘወትር ልማድ አድርጎ ለይስሙላ አገኝ አጣውን ቢቀባጥር እግዚአብሔር አያውቅብኝም በማለት በመንፈስ ቅዱስ መዘበት ነው:: በቄሱ አድሮ ኑዛዜውን የሚሰማውና የሥርየት ኃጢአትንም ምሥጢር እሱው ባወቀ የሚፈጽም መንፈስ ቅዱስ ነውና:: በሐዋርያት ጊዜ ከዚያም በኋላ ለረጅም ጊዜ ኑዛዜ በአደባባይ በሕዝብ ፊት ነበር:: /የሐ.ሥራ 19÷18::/ ካልዕ ቆሮ.7÷11፣ ያዕቆብ 5÷16/ በኋላ ግን ያንዱን ኃጢአት ሌላው ሰምቶ እንዳይሰናከል በማሰብ በምሥጢር ሆነ:: የኃጢአትን ሥርየት በምሥጢር የሚፈጽመው መንፈስ ቅዱስ ቢሆንም አገልግሎቱን የሚፈጽሙ

ካህናት ናቸው:: ይህም ለሐዋርያት በተሰጠው ሥልጣን ነው:: ጌታ በማስተማር ዘመኑ «በምድር ያሠራችሁት በሰማይ የታሠረ ይሆናል፣ በምድር የፈታችሁት በሰማይ የተፈታ ይሆናል» ብሎ ለሐዋርያት ሥልጣንን ሰጥቷቸዋል /ማቴ.16÷19/:: ኋላም በሞቱ ሞትን ደምስሶ በድል አድራጊነት ከተነሣ በኋላ ይህንኑ ቃል እንደገና ደግሞ በሥነ ሥርዓት ሹሟቸዋል /ዮሐ.20÷21/:: ሐዋርያት በዚሁ ሥልጣናቸው ብዙ ሥራ ሠርተዋል:: ለምሳሌ በሐናንያና በሰጲራ፣ በሲሞን መሠርይ፣ በኤልማስ ላይ ያሳዩት ኃይል እግዚአብሔር የማይቀለድበት አምላክ መሆኑን አስመስክሯል /የሐዋ.5÷1–11፣ 8÷20–22፣ 13÷8–12/:: ከሐዋርያት በኋላ የተነሡ የሐዋርያት ወራሽ ኤጲስ ቆጶሳትና ቀሳውስትም ይህን ሥልጣን ወርሰው የክርስቶስን ቤተክርስቲያን ያገለግላሉ::

<u>የምሥጢረ ንስሐ አፈጻጸም፡</u>– በፈጸመው የማይገባ ሥራ ተጸጽቶ ለወደፊቱ ወደዚህ ክፉ ሥራ አልመለስም ብሎ ወስኖ በፍጹም እምነትና በክርስቲያናዊ ተስፋ ተሞልቶ፣ የተሰፋ ስንቁን ቋጥሮ ወደ ቄሱ ይገሰግሳል:: የሠራውንም ጥፋት አንድ ሳይቀር በቄሱ ፊት ይናዘዛል፣ ቀኖናውን ከፈጸመ በኋላ ስርየተ ኃጢአትን ያገኛል:: ወደ ቀድሞው ክርስቲያናዊ ክብሩ ይመለሳል::

መምህረ ንስሐ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን፡– ትውፊት ማንኛውም ምእመን ከአጥቢያው ቄሶች ውስጥ መምህረ ንስሐ መርጦ ይይዛል:: ይህም የነፍስ አባት ይባላል:: ቄሱ ለምእመናኑ የነፍስ አባት፣ የንስሐ አባት፣ መምህረ ንስሐ ይባላል:: ምእመኑም ለቄሱ የነፍስ ልጅ፣ የንስሐ ልጅ ይባላል:: ቄሱ በመከራም ሆነ በደስታ ጊዜ ከነፍስ ልጆቹ አይለይም:: እነሱም የጠም ቆሎ፣ የበዓል ዶሮ፣ የሻሽ ይሉታል:: በቤተክርስቲያናችን ትውፊት መሠረት ምእመናን /የነፍስ ልጆች/ ጥፋታቸውን የሚናዘዙት በምሥጢር በግል ነው:: የቄሱና የምእመናኑ ግንኙነት ይህ ሆኖ ሳለ አሁን ግን ከጊዜ ብዛትና ከትምህርት ማነስ የተነሣ አንዳንድ ምእመናን ሲወልዱ ለማጥመቅ ሲሞቱ ለመፍታት ካልሆነ በቀር ኃጢአትን በየጊዜው ለመናዘዝና ስርየት ኃጢአትን ለማግኘት ወደ ቄሱ ሲሄዱ አይታይም መስቀል ተሳልሞ ይፍቱኝ የሚል ሞልቷል:: ታዲያ ምእመኑ ከኃጢአት ማሠሪያ የሚፈታው ኃጢያቱን ተናግሮ ቄሱ በቤተክርስቲያን ስም የሚሰጠውን ቀኖና ሲፈጽም ነው:: ከዚህ ጋር የኑዛዜ ጉዳይ በቤተክርስቲያናችን እየተረሳ ስለሄደ ብዙ ሰዎች በዓመት አንድ ቀን የስቅለት ዕለት የሚጠበጠቡትንና የሚናዘዙትን ይመስላቸዋል ምሥጢረ ንስሐ የምንለው:: የስቅለት ዓርብ እንደ ተለመደው ሕፃን አዋቂ ሳይባል በየሰበካቸው እየሄዱ ሲሰግዱ ይውላሉ:: ወደየቤታቸው የሚሄዱበት ሰዓት ሲደርስ ቀሳውስቱ የወይራ ቀንበጥ እየያዙ ወደ ሕዝቡ ይወጣሉ:: ሕዝቡ በየተራ ሲቀርቡ እራሳቸውን ወይም ትከሻቸውን በያዙት የወይራ ቀንበጥ ቸብ፣ ቸብ ያደርጉታል /ይጠበጥቡታል:: በዚህ ጊዜ የሕማማት ሳምንት ከገባ ጀምሮ የሠራውን እየተናዘዘ፣ ቀኖናውን ስግደቱን ይቀበላል:: ይህ መቼም ምንጊዜም ጠብቀነው ብንኖር የማያሳፍረን ሃይማኖታዊ ትውፊታችን

ነው። ጥብጣቤው የግርፋት ምሳሌ ነው፣ የምእመኑም ራሱን ጐንበስ አድርጎ ለጠብጣቢ መስጠት፣ ትሕትናንና ታዛዥነትን ያመለክታል። ኑዛዜው ግን ከላይ እንደገለጥነው በሕማማት ሳምንት የተሠራውን መተላለፍ ብቻ የሚመለከት ስለሆነ ይህ በዓመት አንድ ቀን የሚደረገው ኑዛዜና ጥብጣቤ ምሥጢረ ንስሐን በሙሉ አያጠቃልልም።

ምሥጢረ ንስሐ በሌሎች አብያተ ክርስቲያናት በምሥራቅ መለካውያን ሥርዓት የምእመናንን ኑዛዜ ለመስማት የሚችሉት ከኤጲስ ቆጶሳት ልዩ ፈቃድ ያላቸው ቄሶች ብቻ ናቸው። ምእመናኑም የወደዱትን ቄስ መርጠው የነፍስ አባት ለማድረግ አይችሉም፣ የኑዛዜ ሥርዓታቸውም የተወሰነ ነው። ምእመናኑ ቢያንስ በዓመት ሦስት ጊዜ ሥጋውን ደሙን ስለሚቀበሉ /የልደት፣ የትንሣኤ፣ የፍልሰታ ኪዳነ ምሕረት/ ሥጋውን ደሙን ለመቀበል ስምንት ቀን ሲቀራቸው ወደ ናዛዚው ካህን ይገሰግሳሉ፣ የፈጸሙትንም በደል ይናዘዙለታል፤ እሱም የስሕተታቸውን ሁኔታ እያየ የሁለት የሦስት ቀን ቀኖና ይሰጣቸዋል፤ ሲፈጽሙ ሥጋውን ደሙን ይቀበላሉ። ከበድ ያለ ስሕተት የፈጸመ ግን ቅጣቱ ከሥጋውና ከደሙ መከልከል ነው። ለተወሰነ ጊዜ በቀኖና ሰንብቶ ቄሱ ሲፈቅድለት ይቆርባል።

ምሥጢረ ንስሐ በሮማ ካቶሊክ ቤተክርስቲያንም አለ። ኑዛዜ በየጊዜው ነው። ነገር ግን ቀኖና አሰጣጡ ከኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን የተለየ ነው። ተናዛዡ /ተነሳሒው/ ሀብታም ከሆነ ቀኖናውን በገንዘብ ይዋጀዋል/ይለውጠዋል/ ። ናዛዡ ኤጲስ ቆጶስ ወይም ቄስ ገንዘቡን ተቀብሎ የሱን ፈንታ ይጾምለታል ይላሉ። ነገር ግን ይህ በሐዋርያት ቤተክርስቲያን ያልነበረና የሌለ ሰው ሠራሽ ንስሐ ነው፤ ንስሐ በመሠረቱ ወደ ስሕተት ላለመመለስ መወሰን ማለት ነው፤ ተነሳሒው ወደ ፊት ላለመመለስ ከራሱ ጋር ካልታገለ በየጊዜው እያጠፋ ለጥፋቱ ገንዘብ የሚከፍል ከሆነ የቤተክርስቲያን ምሥጢረ ንስሐ የካህናት መነገጃ ሆነ ማለት ነው።

በፕሮቴስታንቱ ዓለም ደግሞ የቀሳውስትን የማሰርና የመፍታት ሥልጣን ስለማይቀበሉ የንስሐንና የኑዛዜን ምሥጢርነትም አያውቁም፤ ተሳስተናል ወይም እንሳሳታለን ማለት በእነሱ ዘንድ ጥፋት ነው።

እግዚአብሔር ይመስገን ይህ ሁሉ ባዕድ ልማድ በእኛ ዘንድ የለም። ትምህርቱ መስመሩን ሳይለቅ ምእመናን እንዲገለገሉበት ካህናትም ምእመናንም የጋራ ጥረት ማድረግ ይገባል። በእኛ ቤተክርስቲያን የንስሐ ጥቅሙና ምሥጢርነቱም ከመጀመሪያው ጀምሮ ሲያያዝ የመጣ ነው፤ ስለኑዛዜና ስለ ቀኖና አሰጣጥም የተጻፉ አያሌ መመሪያ መጻሕፍት አሉን። ለምሣሌ በዋናው የቀኖናው መጽሐፋችን በፍትሐ መንፈሳዊ ፈውስ መንፈሳዊ የተባሉ የስሕተቱን ጠባይና ቀኖናውንም አቀናብረው የሚናገሩ መጻሕፍት አሉን፣ እነዚህንና ሌሎችንም መጻሕፍት መመሪያ አድርገን ምእመናንን ወደ እግዚአብሔር ማቅረብ ለካህናት የተሰየምንበት ተግባር ነው።

## 5. ምሥጢረ ቀንዲል /ዘይት/

ምሥጢረ ዘይት ወይም ጸሎተ ዘይት ቢል በቀና ነበር:: ነገር ግን በግብሩ ቀንዲል ብለውታል:: ቀንዲል /ካንድል፣ ካንዲል/ የላቲን ቃል ነው:: ግሪኮችም ይጠቀሙበታል:: በግእዙም እዚህ ላይ እንደምናየው በጥሬው አስገብተውታል:: ፍጹም መብራት ማለት ነው:: የወይራውን ዘይት በሀገራችን ግን ቅብዐ ኑጉን በጐድጓዳ ዕቃ ሞልተው በውስጡ ቀጭን ፈትል አስገብተው በቤተክርስቲያን በጸሎት ጊዜ ያበሩታል:: ይህ መብራት ቀንዲል ይባላል:: ብርሃኑን የሚሰጠው ዘይቱ ስለሆነ፣ ዘይቱን ቀንዲል /ብርሃን/ ብለውታል:: በዚህም በያዝነው ርእስ ምሥጢረ ዘይት በማለት ፈንታ ምሥጢረ ቀንዲል ያሉት በዚያ ልማድ ነው:: በብሉይ ኪዳን ዘይት የፈውስ ምልክት ነበር፣ በደዌ ዳኛ ባልጋ ቁራኛ ተይዘው የሚሰቃዩ ሕሙማን ወይም በድንገተኛ አጋጣሚ የመቁሰል አደጋ የደረሰባቸው ቁስለኞች ዘይት እየተቀቡ ይፈወሱ ነበር:: /ኢሳ.1÷6፣ ሉቃ.10÷34፣ ራእ.3÷18፣ ማር.6÷13/ ይህ ዘይት የብሉይ ኪዳን ነገሥታትና ካህናት ይቀቡት እንደነበረው ቅብዐ መንግሥትና ቅብዐ ክህነት፣ ወይም በሐዲስ ኪዳን ለጥምቀት ከሚደረገው ቅብዐ ሜሮን ጋር ሞክሼነት የለውም:: ራሱን የቻለ ሕሙማን ሥጋ ብቻ ሳይሆኑ ሕሙማን ነፍስ ኃጥአንም የሚቀቡት ፈውስ የሚያገኙበት ነው::

በሐዲስ ኪዳን ለምሥጢረ ቀንዲል መሠረቱ ሐዋርያው በያዕቆብ ያስተማረው ቃል ነው /5÷14–16::/ :: ሐዋርያት በማስተማር ዘመናቸው ምሥጢረ ቀንዲል ይፈጽሙ ነበርና /ማር.6÷13/ ::ያዕቆብ እንዳስተማረው ይህን ቅዱስ ቀንዲል የሚቀቡ ሰዎች አስቀድመው በንስሐ የተዘጋጁ መሆን ይገባቸዋል:: ለጸሎተ ቀንዲል ቦታ ጊዜ አይለይም:: በቤተክርስቲያን ወይም በሽተኛው በተኛበት አልጋ ዙሪያ ይፈጸማል:: ዕድሜና ሁኔታም አይለይም:: ማንኛውም ምእመን በማንኛውም ሁኔታ ቢሆን ያስፈልገኛል ካለ ንስሐ ገብቶ ኃጢአቱን ተናዞ ቀኖና ተቀብሎ የቀንዲል ምሥጢር ይፈጸምለታል::

የቀንዲልን ምሥጢር የሚፈጽሙት ሰባት ኤጲስ ቆጶሳት ወይም ሰባት ቀሳውስት ናቸው:: እነዚህም ዮሐንስ በራእዩ ያያቸው ሰባት ብርሃናት ምሳሌ ናቸው /ራእ.1÷13/:: ከላይ ያዕቆብ እንዳለው በቤተክርስቲያን ሥርዓት ቀንዲል የሚደረግለት ምእመን በቅድሚያ መናዘዝ አለበት:: ከዚያ በኋላ ምሥጢሩን የሚፈጽሙት ኤጲስ ቆጶሳት ወይም ቀሳውስት ንጹሕ ዘይት አቅርበው ለዚህ የተወሰነውን ጸሎት ያደርሳሉ:: ሰባቱም በየተራ በምእመናኑ ራስ ላይ ወንጌል ያነባሉ:: ይህም የጌታ አንብሮተ እድ ምሳሌ ነው:: ወንጌል ከተነበበ በኋላ ሰባቱም እጃቸውን በራሱ ላይ ጭነው ይጸልዩለታል:: በመጨረሻም በጫፋቸው ጥጥ የተጠመጠመባቸው ሰባት እንጨቶች ይይዛሉ:: ይህንን በየተራ ወደ ተጸለየበት ዘይት እየነከሩ በትእምርተ መስቀል ይቀቡታል፤ በሥርዓተ ሜሮን እንዳየነው አምስቱን ሕዋሳቱን፣ ዓይኑን፣ ጆሮውን፣ አፉን፣ አፍንጫውን እጁን ይቀቡታል:: በዓይኑ አይቶ በጆሮው ሰምቶ፣ በአፉ

ተናግሮ በአፍንጫው አሽቶ በእጁ ዳሶ ለሠራው ኃጢአት ሥርየት እንዲሆነው ሲሉ አምስቱን ሕዋሳት ይቀቡታል።

በምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት የምሥጢረ ቀንዲል አፈፃፀም ሥርዓት ከሞላ ጐደል ይህ ነው። በሩሲያ ቤተክርስቲያን ብቻ በሉቃ ወንጌል 10÷34። የተጻፈውን ይዘው በዘይቱ ላይ ወይን ይጨምሩበታል። ከዚያ በቀር ሌላው አይለወጥም።

በሮማ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን የቀንዲል አፈጻጸም ዓላማው ከምሥራቃውያን የተለየ ነው።

ሀ. ቀንዲል የሚደረገው ለመዳን ሳይሆን ለሞት መዘጋጃ ስንቀ ነፍስ ነው፣ ስለዚህም የሚፈጸመው ለሕሙማን ብቻ ነው። ያውም አእምሮአቸውን ሲስቱና ለመዳን እጅባት ሲባል ነው። (extreme or last unctiony) ይሉታል።

ለ. ከ14 ዓመት በታች ላለ ሕፃን አይደረግለትም።

ሐ. አእምሯቸውን ነካ ለሚያደርጋቸው እብዶች ይሙት በቃ ለተፈረደባቸው እሥረኞችና ለወታደሮችም አይፈጸምላቸውም።

በፕሮቴስታንቱ ዓለም ደግሞ በብሉይ ኪዳን እንደተጻፈው ከደዌ ሥጋ ለመዳንም ሆነ ከደዌ ነፍስ ከኃጢአት ነፃ ለመሆን የቀንዲልን ምሥጢርነት አይቀበሉትም።

በቤተክርስቲያናችን የቀንዲል ምሥጢር አፈጻጸም ከላይ እንደገለጽነው እንደ ሌሎቹ የምሥራቅ አብያተክርስቲያናት ነው። ዓላማውም እንደሮማ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ለመሞት ብቻ ሳይሆን ለመዳን ከኃጢአትም ለመንጻት ነው። በደዌ ነፍስ በኃጢአት ቁራኛ ተጠ ፍሮ ተይዞ፣ በሥጋው ግን ሀብትና ጤንነት አግኝቶ የሚሞላቀቀው ምእመን ከኃጢአት ለመንጻት ኑዛዜና ቀኖና ከዚያም በኋላ ቀንዲል መቀባት ያስፈልገዋል። ደዌ ነፍስ ኃጢአት ሳይኖርበት በደዌ ሥጋ የሚሞላቀቀው ምእመንም ቢሆን በተሳተ በተገደፈ ተናዞ ለመሞትም ቢሆን ለመዳን ቀንዲል መቀባት የቤተክርስቲያን ነባር ትውፊት ነው። አስቀድመን እንደገለጥነው የኢትዮጵያ ኦርቶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የምሥጢረ ቀንዲልን ጥቅም ታስተምራለች። አፈጻጸሙ ግን የተረሳ ይመስላል። በዚህ የቤተክርስቲያን ስጦታ ምእመናን እንዲጠቀሙበት ማስተማርና ማስለመድ የካህናት ፋንታ ነው።

## 6. ምሥጢረ ተክሊል

ተክሊል ማለት «ተከለለ» ተቀዳጀ ከሚለው የግእዝ ግሥ የወጣ ነው። በጋብቻቸው ጊዜ ሙሽራው እንደ ንጉሥ ሙሽራይቱ እንደ ንግሥት ሁነው አክሊል ተቀዳጅተው ነውና። ስለ ምሥጢረ ተክሊል ለማወቅ አሁንም ወደ መጀመሪያው ሰው ወደ አዳም ታሪክ መመለስ ሊኖርብን ነው። በብሉይ ኪዳን በዘፍጥረት እንደተገለጠው ጋብቻ ለአዳምና ለሔዋን የተፈቀደው በእምላካዊ ርኅራሄ በአምላካዊ መግቦት

ነው:: /ዘፍ.2÷18/ በጋብቻ የሰው ዘር እንዲባዛ እግዚአብሔር መፍቀዱም በዚሁ መጣፍ ተገልጧል /ዘፍጥ.2÷18/:: ጋብቻ፣ የባልና የሚስት ተዋሕዶ ነው:: በጋብቻ አንድ አካል አንድ አምሳል ይሆናሉና /ዘፍጥ.2÷18–24/ በአዲስ ኪዳንም የጋብቻ ትምህርት ይህንን ለአዳምና ለሔዋን የተፈቀደውን የጋብቻ ሕግ አይ ቋምም ነበር:: ለምሳሌ መድኃኒታችን በማስተማር ጊዜው ስለ ባልና ሚስት ጉዳይ የፈተና ጥያቄ ላቀረቡት ፈሪሳውያን የመለሰው በዘፍጥረት የተጻፈውን ነው /ዘፍጥ.1÷27፣ 2÷24/:: የሐዋርያት ትምህርትም በጌታ ትምህርት ላይ የተዋቀረ ስለሆነ የጋብቻ ተዋሕዶ፣ ከባድ ምሥጢር መሆኑን ይገለጥ ነበር:: ለምሳሌ ቅዱስ ጳውሎስ ያላገቡት ደናግሉን እንደሱ በድንግልና ቢኖሩ የሚሻላቸው መሆኑን ሲመክር፣ ላገቡት ደግሞ ከዚሁ በላይ ከገለጥነው ጋር የሚስማማ ትምህርት ያስተምር ነበር /ቀዳ.ቆሮ7÷3–4/:: ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ ተብሎ በብሉይ ኪዳን በአዲስ ኪዳን በተነገረው መሠረት /ዘፍጥ.2÷24 ማቴ.19÷5::/ ጋብቻ እንደ አዳምና ሔዋን አንድ ወንድ ላንድ ሴት ነው:: አሕዛብ ግን ጋብቻቸው መመሪያ ስለሌለው የብሉይ ኪዳንንም ትምህርት አካተው ስለማያውቁ አንድ ወንድ ብዙ ሴቶች ያገባ ነበር /polygamy/ ይህንንም ብዙ የማግባት ልማድ በአሕዛብ ብቻ ሳይሆን በሴማውያንም ዘንድ በአንዳንድ ምክንያት አልፎ አልፎ ይደረግ ነበር:: ነገር ግን ለምስክር ያህል ያንድ ላንድ ጋብቻን ጠብቀውና አክብረው የኖ ሩ ከአበው እነ ኖኅ ነበ ሩ /ዘፍጥ.7÷7/

ለዘር መተካትና ለሥጋዊ ፈቃድ መፈጸሚያ ብቻ ሣይሆን ጋብቻ በሃይማኖትም መንፈሳዊ ምሥጢር አለው:: በነቢያት ትምህርት የእግዚአብሔርና የእሥራኤል ግንኙነት ባንድ ሕጋዊ ባልና ሚስት አንድነት ፍቅራቸውም በእግዚአብሔርና በእሥራኤል ፍቅር ተመስሎ ይነገር ነበር /ኢሳ.62÷4–5:: ሆሴዕ 2/:: ከአምልኮተ እግዚአብሔር መራቅና ጣኦት ማምለክ ግን ብዙ ባል ባገባች በሴሰኛ ሴት ተመስሎ ቀርቧል:: ማለት እግዚአብሔር እንደ ሕጋዊ ባል ጣኦትን የሚያመልኩ እሥራኤል እንደ ሴሰኛ ሴት ሁነው ይታያሉ:: ኢሳ.1÷21:: ኤር.3÷1–10 ሕዝቅ.16÷23:: መዝ.73÷27:: ኤር.25÷20:: ሆሴዕ.4÷12::/

በሐዲስ ኪዳንም በክርስቶስና በቤተክርስቲያኑ ያለው ተዋሕዶ በጋብቻ ተመስሏል:: እሱ ሙሽራዋ ቤተክርስቲያን ሙሽራው:: ክርስቲያናዊ ጋብቻን ምሥጢር ሊያሰኘው የበ ቃውም ይኸው ነው:: /ኤፌ.5÷23–32:: ካልዕ ቆሮ11:: ማቴ.9÷15:: ዮሐ.3÷29 ራእ.19÷7:: 21÷9:: 22÷

## የጋብቻ ሥነ ሥርዓት፣

በብሉይ ኪዳን ሕግ የደም ጥልቀት የደም የሥጋ ልደት የሚገናኛቸው ዘመዳሞች አይጋቡም ነበር:: በሃይማኖት ከማይመስሏቸው ጋር እሥራኤል አይጋቡም ነበር:: ዘሌዋ.18-6፣ 21-20፣ 1-21፣ /ዘዳግ.7-3-4/ በሐዲስ ኪዳንም ዝምድናቸው ካልተራራቀ ዘመዳሞች አይጋቡም /ቀዳ.ቆሮ.5-1-5፣ 13::/ ዋርሳ መውረስም ተከልክሏል:: እንዲያውም እነ ዮሐንስ መጥምቅ አንገታቸውን የሰጡት የዋርሳን ሥርዓት በመ ቃወም

ነው። /ማር.6-17 ማቴ.14-1-12/ በሃይማኖትና በዶግማ የማይመሳሰሉም አይጋቡም። ቅዱስ ጳውሎስ እንዳለው ግን ወንዱ ክርስቲያን ሆኖ ሴቷ ባትሆን ወይም እሷ ክርስቲያን ሁና ወንዱ ክርስቲያን ባይሆን እነዚህ ለመጋባት ቢፈልጉ እሱ እሷን አስጠምቆ ወይም እሷ እሱን አስጠምቃ ሊጋቡ ይችላሉ። ያለዚያ ግን ክልክል ነው። ጋብቻውም ከክርስቶስ ፍቅር ሊለይ አይችልምና፣ በክርስቶስ ያልተባረከ ጋብቻ ከዝሙት ይቆጠራል። /ቀዳ.ቆሮ.7-12-17።/

የማግባቱን ያህል ካገቡም በኋ መፍታት ለአሕዛብ ልማድ ቀላል ሲሆን በብሉይ ኪዳን ሕግ ግን ይልቁንም በሥነ ፍጥረት ያልነበረ ነው። መድኃኒታችን ለፈሪሳውያን እንደመለሰላቸው ሙሴ የመፍታትን ሕግ የሠራው /ዘዳግም 24÷1/ በእሥራኤል ክፋት እንጂ ከጥንት ከሥነፍጥረት ስለነበረ አይደለም። ነቢያትም የመፈታትን ሕግ ያወግዙ ነበር/ ሚልክ.2÷14-16።

በአዲስ ኪዳንም ጌታችን እንዳስተማረው በዝሙት ምክንያት ካልሆነ በቀር ከሳች፣ ጠቀረች፣ መከነች፣ ደረቀች ብሎ ሚስትን መፍታት አመንዝራነት ነው። /ማቴ.5÷32፣ ሉቃ16÷18፣ ቀዳ.ቆሮ.7÷10/ ከሁለት አንዱ በሞት ከተለየ ግን በሕይወት የቀረው ለማግባት ይፈቀድለታል። /ሮሜ 7÷2-3/።

የጋብቻ ቡራኬ /ተክሊል/ በአሕዛብ ዓለም ጨርሶ አይታወቅም። በብሉይ ኪዳን ግን ነበር። ይኸውም ግብዣው ከመጀመሩ አስቀድሞ በሙሽሮቹ ፊት ወይን የሞላበት ጽዋ ይቀመጣል በዚያ ላይ ካህኑ ጸሎተ ቡራኬ ያደርስበታል ጸሎቱን እንደፈጸመ ለሙሽራውና ለሙሽራ ዩቱ ያጠ ጣቸዋል። /EDERSHEN I,355/

በሐዲስ ኪዳን የጋብቻ ቡራኬ ሥርዓት በብዙ ቦታ አልተነገረም። ነገር ግን በምሥጢር ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሏት ካለው /ዘፍጥ.1-28/ ከመጀመሪያው ቡራኬና ጌታም የመጀመሪያ ታምራቱን ካሳየበት ከቃናው የሠርግ ቤት ምሥጢር ወስደው የቤተክርስቲያን ሊቃውንት በጋብቻ በዓል ጊዜ የሚፈጸም ልዩ የቡራኬ ጸሎት ሠርተዋል። ለምሳሌ በሁለተኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ ላይ የነበረው ሐዋርያዊ የቤተክርስቲያን አባት አግናጥዮስ፣ የክርስቲያኖች ጋብቻ በኤጲስ ቆጶሱ ፈቃድ ኤጲስ ቆጶሱ ባለበት እንዲፈጸም ሥርዓት ሠርቷል። /አግናጥዮስ ለፖሊካርፖስ ከጻፈው መልእክት አምስትን ይመለከቷል።/ ሌላው የቤተክርስቲያን አባት ጠርጠ ሉስ ደግሞ ይህንኑ ትምህርት በመደገፍ «የክርስቲያኖች ጋብቻ አማናዊ የሚሆነው በኤጲስ ቆጶሱ ፈቃድ የሆነ እንደሆነ ነው፣ ያለበለዚያ ግን ጋብቻ አይባልም» ይል ነበር። ጠርጠሉስ:– de pudiciti –4 de momogamy/ እንዲያውም ይኸው የቤተክርስቲያን ሊቅ «ቤተክርስቲያን ሳታውቀው የሚፈጸም ጋብቻ ሁሉ፣ ዝሙት እንጂ ጋብቻ አይባልም» ይላል። ስለዚህ እንዲህ ያለው ጋብቻ መፍረስ እንዳለበት ጠርጠሉስ አስተምሯል። ከዚህም በማያያዝ በየዘመኑ የተነሡ ሊቃውንት ሁሉ ስለ ክርስቲያናዊ ጋብቻ ሰፊ ትምህርት አስተምረዋል። ብዙ መጻሕፍትም ጽፈዋል። በትምህርተ አበው መሠረት ተክሊል ከቅዳሴና ከቁርባን ጋር የተያያዘ ነው። ሙሽሮቹ

ቆመው አስቀድሰው ሥጋውን ደሙን ይቀበላሉ፣ ከዚያም በሚዜዎቻቸውና በእድምተኞች ታጅበው ወደ ሙሽራው ቤት ይጓዛሉ። ከዚያ በኋላ የሚፈጸመው ሁሉ እንደየ — ሀገሩ ባሕልና ልማድ ነው። አምብሮስዮስ የተባለው የቤተክርስቲያን አባት በሀገረ ስብከቱ /በሚላኖ/ ስለ ክርስቲያኖች ጋብቻ ሲገልጥ እንዲህ ይል ነበር፣ «ከቤተክርስቲያን ተመልሰው ወደ ሙሽራው ቤት ይሄዳሉ፣ ከበሩ ሲደርሱ ሙሽራይቱ ጠጉሯን ወይም የጠጉሯን ማሠሪያ ሻሿን ዓይነ ርግቧን ትፈታለች፣ የባሏ እንጂ የሌላ አለመሆንዋን ለመግለጥ ነው። /ቀዳ.ቆሮ 11÷2-16/ እሱም የቤቱን ቁልፍ ያስረክባታል። የቤቱ ባለቤት እሷ መሆንዋን ለመግለጥ ነው» /Ambr. Epist 6÷3/

በምሥራቅ ሰሪያ የሚኖሩ ክርስቲያኖች ደግሞ ሥርዓተ ተክሊሉን በቤተክርስቲያን ከፈጸሙ በኋላ ወደ ቤታቸው ተመልሰው የሚፈጽሙት ተጨማሪ ሥርዓት አላቸው። በጽዋ ወይንና ውኃ ቀላቅለው ይጸልዩበታል። ከጸሎቱ በኋላ ከመቃብረ ሰማዕታት አፈር ዘግነው አምጥተው ከጋብቻ ቀለበት ጋር ወደ ጽዋው ይጨምሩታል፣ ሙሽራውና ሙሽራይቱ ከዚህ ጽዋ ፉት ፉት ብለው ቀምሰው ቀለበቱን በጣታቸው ያገቡታል፣ በራሳቸው ላይ የሚደረገው ተክሊል ደግሞ፣ ቀይ ነጭና ሰማያዊ ፈትል አንድ ላይ ገምደው ነው፣ ዛሬም በአርመን ቤተክርስቲያን ለተክሊል የሚጠቀሙበት ይህንን የሐር ገመድ ነው።

የተክሊል አፈጻጸም ሥርዓት በእኛ ቤተክርስቲያን ከሌሎች አብያተክርስቲያናት ጋር የሚመሳሰልበትም የሚለያይበትም ጠባይ አለው። ስለ ተክሊሉ አፈጻጸም ከማውሳታችን በፊት ቤተክርስቲያኒቱ ስለ ጋብቻ የምታስተምረውን ትምህርት እንገልጣለን። ተክሊል በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሥርዓት በብሉይ ኪዳንና በአዲስ ኪዳን ትምህርት ላይ የተመሠረተ ነው።

ስለ አንድ ለአንድ ጋብቻ /momogamy/ በሃይማኖት ወይም በዶግማ ከማይመስሉት ጋር አለመጋባት፣ ጋብቻ ያለ በቂ ምክንያት ማለት በዝሙት፣ በሞት፣ ምክንያት ካልሆነ በቀር የማይፈርስ መሆኑን፣ ከሌሎች አብያተክርስቲያናት ጋር አብራ ታስተምራለች። ይልቁንም ሥጋዊም ሆነ መንፈሳዊውን ተዛምዶ ለመጠበቅ ሲባል እስከ ሰባት ትውልድ ድረስ ያሉ ዘመዳሞች ለመጋባት አይችሉም። ለምሣሌ:-

ሀ. ወደ ላይ ልጅ፣ የአባቱን፣ የአያቱን የቅድመ አያቱን፣ ሚስት፣ ልጁን፣ እኅቷን፣ እናቷን፣ አያገባም።

ለ. ወደ ታች አባት፣ የልጁን የልጅ ልጁን፣ ሚስት፣ ልጁን፣ እኅቷን፣ እናቷንና፣ አያቷንም አያገባም። በኦሪት ዘሌዋውያን እንደተጻፈው፣ የወንድም የእኅት የአክስትና፣ የአጐት፣ የአማትና የምራት የዋርሳና የአያት፣ ጋብቻ ክልክል ነው /ዘሌዋ.18÷6-21። 20÷1-21/። መንፈሳዊ ተዛምዶም የክርስትና ልጅ ወይም የጡት ልጅ፣ የቈሲስን አባቱን ሚስት፣ ልጁን፣ የልጅ ልጁን፣ እኅቱን፣ አያገባም፣ አባቱም የክርስትና

ወይም የጡት ልጇን ፣እናቱን፣ እኅቱን፣ የእኅቱን የወንድሙን ልጅ አያገባም /ፍትሕ.መንፈሳዊ/፡፡

እነዚህን ከዚህ በላይ የዘረዘርናቸውን ጋብቻን የሚከለክሉ ገደቦች ጠብቀው ከአሥራ አምስት ዓመት ያላነሰ ዕድሜ ያላት ድንግል ከአሥራ ስምንት ዓመት ያላነሰ ዕድሜ ያለው ድንግል ጎበዝ፣ በወላጆቻቸው አማጭነት፣ ያለዚያም በቤተሰብ ተጠያይቀው ካልሆነም ራሳቸው ተዋውቀውና ተፈቃቅደው ጋብቻን ለመፈጸም ይችላሉ፡፡ ከጋብቻው ቀደም ሲል ግን ሁለቱ እጮኛሞች በወላጆቻቸውና በመምህረ ንስሐቸው የውዴታ ቃላቸውን ከሰጡና ፈቃደኛነታቸውን ከገለጡ በኋላ፣ ወደቤተክህነት የተክሊል ክፍል ሄደው የጋብቻ ደንብ የሚያዘውን ያሟላሉ፡፡ የሠርጉ ቀን ሲደርስ ከቤተክህነቱ የተክሊል ክፍል የተሰጣቸውን ማስረጃ በሰበካቸው ላለው የቤተክርስቲያን አስተዳዳሪ ያቀርባሉ፡፡ ከዚህ በኋላ የተክሊሉ ሥርዓት ይፈጸማል፡፡

ከተክሊሉ ቀደም ሲል የሚፈጸመው የቀለበት ቃል ኪዳን ነው፡፡ የቀለበት ቃል ኪዳን የሚፈጸመው ቢቻል በቤተክርስቲያን ባይቻል ደግሞ በልጃገረዲቱ ቤት ነው፡፡ በሁሉም የነፍስ አባት ቄስ አይለይም፤ ሥራውን የሚመራው እሱ ነውና፡፡

የክርስቲያኖች ጋብቻ ብዙውን ጊዜ የሚፈጸመው እሑድ ነው፣ በቤተክርስቲያን ውስጥ ያለው የተክሊል አፈጻጸም ሥርዓት፣ ቅዳሜ ለእሑድ ከሌሊቱ በዘጠኝ ሰዓት ሙሽራው ከሚዜዎቹና ከቤተዘመዱ ጋር፣ ሙሽራይቱም ከዘመዶቿ እና ከሚዜዎቿ ጋር ወደ ቤተክርስቲያን መጥተው የተመደበላቸውን ቦታ ይይዛሉ፡፡ ሙሽራው ከነተከታዮቹ በሰሜናዊ ማዕዘን፣ ሙሽራይቱ ከነተከታዮቿ በደቡባዊ ማዕዘን ይቆማሉ፡፡ ተክሊሉ የሚፈጸምበት ሰዓት ሲደርስ በምዕራቡ በኩል ከመካከለኛው ክፍል በድርገት መውረጃው በቅድስቱ የተክሊል መፈጸሚያው ክፍል ይዘጋጃል፡፡ ሁለቱም ሙሽሮች ባንድ አግዳሚ መቀመጫ ያለዚያም በሁለት ወንበሮች ግራና ቀኝ ይቀመጣሉ፡፡ ሙሽራይቱ የምትቀመጥ በቀኙ በኩል ነው፡፡ በፊት ለፊታቸው የሚቀዳጁት አክሊል የሚቀቡት ዘይት የሚለብሱት ልብሰ ክህነት እነዚህ ሁሉ በሙሽሮቹ ፊት በጠረጴዛ ይቀመጣሉ፡፡ ከዚህ በኋላ የተክሊሉ ጸሎት በሙሽሮቹ ላይ የሚጸለየው ጸሎት ሲፈጸም ቄሱ ባርኮ ያለብሳቸዋል፣ የዘይቱ ጸሎት ሲፈጸም ግንባራቸውን በትእምርተ መስቀል ይቀባቸዋል፡፡ የአክሊሉ ሥርዓት ሲፈጸም ባርኮ በየራሳቸው ላይ ያደርግላቸዋል፡፡ ከዚህ በኋላ ማጠቃለያ የቡራኬ ጸሎት አድርሶ ሲፈጸም ጸሎተ ቅዳሴው ይጀመራል፡፡ አስቀድሰው ሥጋውን ደሙን ይቀበላሉ፡፡ ቃል ኪዳናቸውን በሥጋውና በደሙ ያጸናሉ፤ ያለቁርባን ተክሊል፣ ተክሊል አይባልም፡፡ መላውን የተክሊል ሥርዓተ ጸሎት በመጽሐፈ ተክሊል ይመለከቷል /መጽሐፈ ተክሊል፣ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ፣ 1956ዓ.ም. ገጽ 15-17/ በዝሙት፣ በሃይማኖት በሞት ምክንያት ካልሆነ በቀር ባልና ሚስት እንዳይለያዩ ቤተክርስቲያናችን ታስተምራለች፡፡ ከላይ ከተጠቀሱት ምክንያቶች ባንዱ ቢለያዩ ግን ለወንድም ሆነ ለሴት እንደገና ማግባት ይፈቀዳል፡፡ ይህ እስከ ሦስት ጊዜ ይሆናል፡፡ ከዚያ በላይ ግን

እንደ ዝሙት ይቆጠራል። ተክሊል በሌሎችም አብያተ ክርስቲያናት የተለያየ አፈጻጸም አለው፤ በምሥራቅ መለካውያን ዘንድ የተክሊል ሥርዓት በጣም ጥብቅ ነው፤ የተክሊሉን ፈቃድ የሚሰጥ ጳጳሱ ነው፣ ጳጳሱም ካልተገኘ የሰበካው ካህን ለጳጳሱ ጽ/ቤት አሳውቆ ያስፈቅዳል። ማዘጋጃ ቤት የጋብቻውን ውል የሚያጸድቀው የቤተክርስቲያኑን ማኅተምና ፈቃድ የሰጠውን ኤጲስ ቆጶስ ፊርማ ካረጋገጠ በኋላ ነው። ጋብቻ በእነሱ ዘንድ ሃይማኖታዊ ምሥጢርነት የያዘ ቢሆንም፣ በማኅበራዊ ኑሯቸው ደግሞ የቤተሰብ መመሥረቻ ውል ስለሆነ በወንዱና በሴቷ ፈቃድ ብቻ የሚፈጸም ሳይሆን በሕገ መንግሥታቸው ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚደረግለት ተቀዳሚ ሕግ ነው፤ ያለ ጥሩ ጋብቻ ጥሩ ዜጋ ማፍራት አይቻልምና። ይህን የመሰለ አብሮ መሥራት ለቤተክርስቲያንም ለመንግሥትም ጠቃሚ ነው። ከተጋቡ በኋላ መፋታት ክልክል ሲሆን በሁለቱ ማለት በባልና ሚስቱ ስምምነት ሊፋቱ ይችላሉ። ይህንንም የሚፈቅድ ኤጲስ ቆጶስ ብቻ ነው። ማግባት ግን ቢበዛ ከሁለት ጊዜ አይበልጥም። በሮማ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ጥብቅ የጋብቻ ሕግ አላቸው። መፋታት ፈጽሞ ክልክል ነው። ነገር ግን ሕጋቸው መፋታትን ቢያግድም የሃይማኖት ሥርዓት እምነት እንጂ ሕግ ስለማያግደው ከጋብቻው ውጭ ብዙ ስሕተቶች የሚፈጸሙ መሆናቸው ግልጽ ነው። በፕሮቴስታንት ቤተክርስቲያን ተክሊል ምሥጢርነት የለውም። ባልና ሚስት ካልተስማሙ በማናቸውም ጊዜ መፋታት ይፈቀዳል።

ከመጀመሪያ እስከአሁን ስለ ሰባቱ ምሥጢራት አፈፃፀም በኢትዮጵያና በሌሎችም አብያተ ክርስቲያናት እንዴት እንደሆነ ገልጠ ናል። ቤተክርስቲያናችን በዘመናት ሁሉ ለምእመናኗ የምታስተምረው በዚህ እንደገለጥነው ነው። ምእመናኑ ግን እነዚህን ምሥጢራት ሙሉ በሙሉ አይጠቀምባቸውም። ይህም የሆነበት ምክንያት ኢትዮጵያ ሀገራችን ብዙ ጊዜ በጠላት ስለተወረረች ይልቁንም ከግራኝ ወረራ በኋላ ብዙ ክርስቲያናዊ ትውፊት ስለተደመሰሰ ነው። ከነዚህ ከሰባቱ ምሥጢራት ጥምቀት፣ ሜሮን፣ አዲስ ተጠማቂን ወዲያው ማቁረብ፣ አልተረሱም። ኃጢአትን በየጊዜ መናዘዝ ምሥጢረ ቀንዲልና የተክሊል ጋብቻ ተረስተው አልፎ አልፎ ካልሆነ በብዛት ሲፈጸሙ አይታዩም። በርግጥ ዲያቆናት ሲያገቡ በተክሊል ነው። ከምእመናንም አንዳንድ አይታጡም። ምሥጢረ ቁርባንም በመፍራት ብዙዎቹ ሲሸሹት ይታያሉ። በእርግጥ ሲጠ መቁ ጀምረው አካለ መጠን እስኪደርሱ ይቆርባሉ። ከዚያ በኋላ ግን ብዙዎቹ እስኪያረጁ ድረስ አይቆርቡም፤ ለዚህም የሚሰጡት ምክንያት በሕይወታቸው ውስጥ ስሕተት ሊፈጸም ይችላል ነው። ታዲያ ግን ኃጢአ ታቸውን በንስሐ እየታጠቡ ቢቀበሉት ከተጨማሪ ስሕተት ይጠብቃቸው ነበር። አንዳንዶቹ በንስሐ እየተመለሱ ይቆርባሉ። ያም ሆነ ይህ እዚህ ላይ ያሰፈርነው ስለ ምሥጢራተ ቤተክርስቲያን የቤተክርስቲያናችንን መሠረታዊ ትምህርት ነው።

ይትባረክ እግዚአብሔር